## አንድ፡አንድ፡ ጥቅሶች፡ ከመጽሐፍ፡ቅዱስ፡

### የእግዚአብሔር፡ቃልነቱ፦

ትንቢት፡ከቶ፡በሰው፡ፈቃድ፡አ
ልመጣምና፡ዳሩ፡ግን፡በእግዚአ
ብሔር፡ተልከው፡ቅዱሳን፡ሰዎች፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ተነድተው፡ተና
ገሩ። ፪ጴጥ፡ ፩ ÷ ፳፩።

«...ስለዚህ፡የመልእክትን፡ቃል፡
እርሱም፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡
ከእኛ፡በተቀበላችሁ፡ጊዜ፡በእው
ነት፡እንዳለ፡በእናንተ፡በምታም
ኑ፡ደግሞ፡እንደሚሠራ፡እንደ፡እግ
ዚአብሔር፡ቃል፡እንጂ፡እንደ፡ሰው
ቃል፡አድርጋችሁ፡ስላልተቀበላች
ሁት፡እኛ፡ደግሞ፡እግዚአብሔርን፡
ሳናቋርጥ፡እናመሰግናለን።» ፩
ተሰ፡ ፪ ÷ ፲፫።

### እውነትነቱ

«ቃልህ፡እውነት፡ነው።» ዮሐ፡፲፯÷፲፯

«የቃልህ፡መጀመሪያ፡እውነት፡ነው።» መዝ
፻፲፱ ÷ ፻፷

«ጌታየ፡እግዚአብሔር፡ሆይ፡አሁንም፡
አንተ፡አምላክ፡ነህ፡ቃልህም፡እውነት፡
ነው።» ፪ሳሙ፡፯÷፳፰።

«በዙፋኑም፡የተቀመጠው፡እነሆ፡ሁ
ሉን፡አዲስ፡አደርጋለሁ፡አለ፡ለእኔም
እነዚህ፡ቃሎች፡የታመኑና፡እውነተ
ኞች፡ናቸውና፡ጻፍ፡አለኝ።» ራእ
፳፩÷፭።

### ዘለዓለማዊነቱ፦

«ሰማይና፡ምድር፡ያልፋሉ፡ቃሌ፡
ግን፡አያልፍም።» ሉቃ፡፳፩÷፴፫

«አቤቱ፡ቃልህ፡በሰማይ፡ለዘለዓ
ለም፡ይኖራል።» መዝ፡፻፲፱÷፹፱

### መሪነቱ÷

«ሕግህ፡ለእግሬ፡መብራት፡ለመንገዴ
ም፡ብርሃን፡ነው።» መዝ፡፻፲፱÷፻፭

«ቃሉን፡ግን፡የሚጠብቅ፡ሁሉ፡በእ
ርሱ፡የእግዚአብሔር፡ፍቅር፡በእ
ውነት፡ተፈጽሞአል። ፩ዮሐ፡፪÷፭

መጽሐፍ፡ቅዱስ፡የእግዚአብሔር
እውነት፡ነው። የሰውን፡ኀጢአተኛ
ነትና፡ክርስቶስ፡በመስቀል፡ሳይበ
ከረለው፡መሥዋዕትነት፡የሚገ
ኘውን፡ጽድቅ፡ያመለክታል። እግዚአብ
ሔር፡በዚህ፡መጽሐፍ፡የገለጠልንን፡እ
ውነት፡እንድንቀበል፡ያስገነዝበናል።

«እውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ፡ቃሌን
የሚሰማ፡የላከኝንም፡የሚያምን፡የዘ
ለዓለም፡ሕይወት፡አለው።» ዮሐ፡፭÷፳፬

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
☎ 151233 ፖ.ሣ.ቁ. 1252 አዲስ አበባ
☎ 113455 ፖ.ሣ.ቁ. 700 አሥመራ

# ትንሣኤ



ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፶፯ ሰኔ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ተዋም ር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ክርስቲያን በኅብረተሰብእ መካከል | ፪ |
| ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምሕረት | ፫ |
| ሰላም ለሁላችሁ | ፬ |
| የሳንባ ነቀርሳ | ፮ |
| ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያን | ፯ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፱ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፲ |
| ጨውና የሕይወት ጣዕሙ | ፲፪ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፲፬ |
| ወጣቶች በጥንታዊ ት ቤት | ፲፭ |
| ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ | ፲፰ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፳፩ |
| የቤተ ሰብእ ዓምድ | ፳፫ |


# ደብዳቤዎች

ለኢ.ኦ.ተ.ሐ. ድርጅት
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ መንፈሣዊ ሰላምታዬን ለድርጅቱ እያቀረብኩ የሚከተለውን አስተያየት አቀርባለሁ ።

ይኸውም በመጀመሪያ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አደረጋችሁት፤ ያለውን ቃል በመዘንጋት በየአፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢና ውጭ የሚደረጉ የንግድን ሁኔታዎች በሚመለከት ሲሆን ቅድስት ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች አምላካቸውን የሚያመልኩባትና በጸሎት የሚያገኙባት የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ስትሆን እሷን በማለት የሚሰበሰቡ ምዕመናን በሙሉ ሊጠቀሙባት እንጂ ሊጐዱባት አይገባም ። ነገር ግን አምላካቸውን አወድሰውና ሥርየተ ኃጢአትን አግኝተው ወይም ተሳልመው ሲመለሱ በቤ/ክ/ግቢና ውጭ ወይም ከግንቡ ሥር በመቀመጥ ከአንገት በላይ ታቦት ከአንገት በታች ጣዖት የሚያመልኩ የሚያውቁና የማያውቁ ሥጋዊ መንፈስ ያጠቃቸው ወገኖችን ከቤ/ክ. ሲመለሱ ነጭ ሽቶ (ሃሪቲ) ከርቤ ፣ ማሽላና እንዲሁም የመሳሰሉትን ቡናውና ቃሪያው ምስሩ ሌላም ሳይቀር ከፍተኛ ንግድ እየተካሄደ ይታያል ። ታዲያ ይህ ስሕተት ሲሠራ ማየቴ ክርስቲያናዊ ግዴታን ያለመፈጸም መስሎ ስለታየኝና እኔም ሲገዙ የማያቸውን በመውቀስና ማድረግ እንደሌለባቸው በመሃይምን አቅሜ ሳስጥልና ትምህርት ስሰጥ እንዴት ከገነት ወደ ሲኦል እያልኩ በተለይ ሴቶች እህቶቼን ባለኝ አጋጣሚ ጊዜ ለማስተማር ሞክሬአለሁ ።

ነገር ግን የኔ ተግባር ብቻ ስላልሆነ ቤተክርስቲያናችን ታፍራና ተከብራ መኖር ሲገባት የዛር የሽቀጥ መሸመቻ ቦታ መሆን እንደሌለባት ለየአድባራቱ ኃላፊዎችና እንዲሁም ትምህርት በሰፊው በከብረ በዓላት ጊዜ ትምህርት መስጠትና ማስተማር እንዳለባቸው ለየመምህራኑ እንዲነገርልኝና በቤ/ክ/ አካባቢ ሲሸጥ እንዳይገኝ በዘበኛ ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግ ሳሳስብ ጥያቄዬ ተቀባይነት አግኝቶ ይህ ድርጊት ተግባራዊ እንደሚሆን በአምላኬ በመተማመን ላሳስብ ተገድጃለሁ ።

ከደ/ገ/ቅ/አ/ቤ/ክ/የቅ/አ
መንፈሣዊ /አ/ ማህበርተኛ ውስጥ
አንድዋ መምህርት ሠናይ አስፋው

መምህርት ሠናይ አስፋው እርስዎ ከላይ የተጠቀሱት ተግባር መፈጸም እንደሌለበት በጋዜጣና በመጽሔት ደጋግመን ያሳሰብን ሲሆን ጻሩ ግን ተቀባይነት ባለማግኘቱ እስከአሁን የተደረገ እርማት የለም ምን አልባት መጽሔትና ጋዜጣችን ባይደርሳቸው እንደሆነ አልገባንም አሁንም የሰሚ ያለህ እያልን እርስዎ የላኩልንን አስተያየት እንዳለ አውጥተነዋል ፣ መምህርት ስለ መልካም አስተያየትዎ በእግዚአብሔር ስም ምሥጋና እናቀርባለን ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ ሥራችሁ የተቃና እንዲሆን እመኛለሁ ።

እኔም ከመጽሔቱ ደምበኞች አንዱ በመሆኔ በትምህርቱ ተደስቻለሁ አሁን ልጠይቅ የፈለግሁት ጻድቁ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አገራቸው ታሕታይ ግብጽ ንሂሣ አባታቸው ስምዖን እናታቸው አቅሌስያ ከተባሉት ተወልደው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በየአህጉሩ እየተዘዋወሩ ማስተማራቸውንና ከገዳማትን ከመድኃኒታችን በተሰጣቸው ጸጋ ታምራት ሠርተው ማረፋቸውን መጋቢት ፭ ቀን ፻፫ ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ድምጽ ተዋህዶ ጋዜጣ ለመረዳት ችያለሁ ።

አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሞት የተለዩበት እረፍታቸው የት እንደሆነና አጽማቸው ያረፈበትን ጋዜጣው አላብራራውም ከአንዳንድ ሰዎች የምሰማው እረፍታቸው ሰዶ ምድረ ከብድ ነው ተብሎ በቃል ቢነገርም በተጨባጭ ማስረጃ ለማረጋገጥ ባለመቻሌ ከአንዳንድ ሰዎች ለሚቀርበው ክርክር ወሣኝነቱ ጠይቶ መረዳት መሆኑን ስለ አመንኩበት እረፍታቸውና አጽማቸው ያረፈበት ምድረ ከብድ እንደሆነ ወይም በሌላ ቦታ ተብራርቶ በትንሣኤ መጽሔት እንዲረጋገጥልኝ ።

፪ኛ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወንድ ልጅ በ፵ ቀኑ ሴት ልጅ በ፹ ቀኗ ጥምቀተ ክርስትና ይጠመቃሉ ወላጆች ግን በተወሰነላቸው ቀናት ክርስትና ሳያጠምቁ ከዓመት በላይ ያቆዩዋቸውና ሳይጠመቅ ሕጻኑ ይሞታል አባትና እናት ክርስቲያን ናቸው በክርስትና ሳይጠመቅ የሞተው ልጅ ክርስቲያኖች በሚቀበሩበት በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ ሊቀበር መቻል አለመቻሉን በመጽሔቱ ተብራርቶ እንዲረጋገጥልኝ በናፍቆት እጠባበቃለሁ ።

ባላምበራስ በቀለ ደንበለው
አርሲ ኮፈሌ ከተማ

ባላምበራስ በቀለ ደንበለው በተቀዳሚ የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆን በተደጋጋሚ ስለላኩልን አስተያየትና መንፈሳዊ ሰላምታ እናመሰግናለን ወደፊትም ይህ መንፈሳዊ ስሜት እንዳይለየዎ ከልብ እንመኝልዎታለን ።

ከዚህ ቀጥሎ ላቀረቧቸው ጥያቄዎ መልሶቹ እነሆ ፣

፩ኛ/ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የሞቱት በምድረ ከብድ ነው አጽማቸው ያረፈበት ቦታ ግን የት እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።

መጽሐፈ ገድላቸው ሲሞቱ መላእክት እንደገነዟቸው ሲገልጽ የተቀበሩበትን ቦታ ግን የሚያውቅ የለም ይልና በኢየሩሳሌም ነው የሚሉ አሉ በምድረ ከብድም ነው የሚሉም አሉ በማለት አሳቡን ይደመድማል ፣ ስለዚህ ገድላቸ

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእስ አንቀጽ

# ክርስቲያን በኅብረተ ሰብ መካከል

### ፩. በሥራ መስክ

ክርስቲያን በሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ሁሉ መልካም አርአያነት ይፈለግበታል ።

ከሁሉ በፊት ክርስቲያን በሚኖርበት ኅብረተሰብእ መካከል ሠርቶ ቤተ ሰቡንና ራሱን እንዲረዳ እንጂ በሌላው ድካም መኖር እንደማይገባው በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞአል ። በዚህም አይነት ኑሮው ራሱን ለሌሎች መልካም ምሳሌ ያደርጋል ። (፪ ተሰ. ፫.፯-፲)

ክርስቲያን ለሚኖርበት ኅብረተሰብ ጨው ነው ፣ ስለዚህም በበጎ ምግባሩና በቀና እምነቱ ሌላውን እንዲለውጥ ይፈለግበታል ። ክርስቲያን ለሚኖርበት ኅብረተሰብ የመቅረዝ ላይ መብራት ነው ። በሚሠራበት የሥራ መስክ ሁሉ ሌሎች መልካም ሥራውን አይተው እግዚአብሔርን ያመሰግኑታልና ።

ክርስቲያን በተመደበበት የሥራ ክፍል ሁሉ አሠሪውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንና ሥራውን በማክበር ይሠራል ። በሥራው ፍጹም ታማኝነትንና ፈቃደኛነትን ትጋትንም ያሳያል ። "ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ" የተባለውን ቃል ለክርስቲያናዊ ሕይወቱ መመሪያ አድርጎ በትጋቱ ለሌሎች ሁሉ አርአያ ሊሆን ይገባዋል ።

እውነተኛ ክርስቲያን የሥራ ሰዓትን በማክበር ረገድ ምሳሌ መሆን እንዳለበት ያስተውላል የሥራ መጀመሪያ ሰዓቱን አያሳልፍም ። ሰዓት ሳይደርስ በመውጣትም የሥራ ጊዜውን አይሠርቅም ። ለሌሎችም ዕንቅፋት አይሆንም ። ነገር ግን ሥራ ክቡር መሆኑን ዘንግቶ በሃይማኖታዊ ሥርዓት እያሳበበ የሥራ ሰዓቱን የማያከብር ቢኖር በሃይማኖቱም በኩል ታማኝነት አይኖረውም ።

ከክርስቲያን የሚፈለገው ለሥራ ሰዓት መገዛት ብቻ አይደለም ። ወደ ሥራ ክፍሉም ከገባ በኋላ የተመደበለትን ዕለታዊ ሥራ መሥራት እንጂ የግል ሥራውን መሥራት እንደማይገባው ማስተዋል ይኖርበታል ። የተቀጠረበትን የመንግሥት ወይም የሕዝብ ሥራ ቸል በማለት የግል ሥራውን የሚሠራ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ መጥፎ ምሳሌ ከመሆኑም በላይ ክርስቲያንነቱን ያስነቅፋል ። ክርስቲያን ለእግዚአብሔርም ለሰውም ታዛዥ እንደመሆኑ መጠን ለእግዚአብሔር ክብር በሚሠራበት ጊዜ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ለሰዎችም ሲሠራ ከፍተኛ ማስተዋል ሊያደርግ ይገባዋል ።

ለምሳሌ ተቀጥሮ በሚሠራበት መንግሥታዊም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ መሣሪያዎችን ለግል ጥቅሙ ከማዋል መጠንቀቅ ይኖርበታል ። ነገሩን ግልጥ ለማድረግ የመንግሥት ወይም የድርጅት መኪናዎችን ለግል ሥራ ማሽከርከር ነዳጁን ወደ ግል መኪና መገልበጥ በጽሕፈት መሣሪያዎች የግል ጉዳዩን መጻፍ ሥርየት የሌለው ኃጢአት ስለሆነ ክርስቲያን እንዲህ ያለውን መፈጸም የማይገባው ከመሆኑም በላይ ሌሎች ሲያደርጉ ቢያይም ክርስትያናዊ ምክር መስጠት እንጂ ቸል ማለት አይገባውም ፣ ኃጢአተኛ ማለት ኃጢአትን የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በሌላው ኃጢአት የሚስማማም ኃጢአተኛ ነው" ተብሎአልና ።

### ፪. በገንዘብ አጠቃቀም

እውነተኛ ክርስቲያን ገንዘቡን በትክክለኛ መንገድ በማዋል ይጠቀማል ግን በገንዘብ ፍቅር አይሸነፍም ሕይወቱ የተመሠረተ በገንዘብ አለመሆኑን ያውቃል ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የሰው ሕይወቱ በገንዘቡ ብዛት አይደለም" ያለውን ያስተውላል ። አዎ ሕይወት የብርና የወርቅ የብዙ ሀብትና ንብረት ትርፍ ወይም ውጤት አይደለም ።

በመሠረቱ ገንዘብ በዚህ ዓለም ጥሩ አገልጋይ ነው ። በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ገንዘብ ክፉ ጌታ ነው ። ስለዚህ ክርስቲያን በገንዘቡ መገልገል እንጂ የገንዘብ አገልጋይ መሆን እንደማይገባው ተጽፎአል ። ገንዘብ ራሱ ኃይል ነው ። ሆኖም ክርስቲያን በገንዘብ ተማርኮ ለኃይሉ መገዛት አይኖርበትም ። ለገንዘብ ተገዥ የሆነ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ሊያገለግል አይችልም ።

ባለጸጋ ክርስቲያን በገንዘቡ ምክንያት ኃጢአተኛ አይደለም ። ገንዘብም ራሱ ኃጢአት አይደለም ። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን አይልም ። ግን ገንዘብ ኃጢአት የሚሆነው በአጠቃቀሙ በኩል ስለሆነ ክርስቲያን ስለ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ።

እውነተኛ ክርስቲያን የራሱን ገንዘብ በማይገባ አያባክንም ። የሌሎችንም አይመኝም አይሠርቅም አያሠርቅም ።

ክርስቲያን የቻለውን ያህል እንዲረዳ እንጂ ገንዘቡን አበድሮ እንደዚሁም ተበድሮ ባለ ዕዳ እንዲሆን አልተፈቀደለትም ። (ሮሜ. ፲፫.፰)

ለማጠቃለል ያህል ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያስተውሉት የሚገባው ነገር በተሠማሩበት መንግሥታዊ ወይም ድርጅታዊ የሥራ መስክ ትጋትንና ቅንነትን የሥራ ሰዓትንም ማክበር እንዳለባቸው ነው ። ከዚህም ጋር በገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ረገድ ፍጹም ታማኝ ሆኖ መገኘት የክርስቲያንነታቸው የእውነተኛ ሰውነታቸውና የመልካም ምሳሌነታቸው ማኅተም ነው ።



# ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምህረት

እነሆ አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ ፣ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ ትን. ዘካርያስ ፫፣፬፤

መላእክት ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ ለሰዎች ብዙ አገልግሎትን ሰጥተዋል ። መንፈሱ ተራቁቶ ፣ በፍርሀትም ተውጦ የሚንቀጠቀጠውን ተስፋ የቆረጠ በማጥናናት ፣ በማረጋጋት ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቁታል ።

በተለይም ቅዱስ ሚካኤል ከእግዚአብሔር ምህረትን ወደ ሰዎች በማድረስ ለጥፋት የተቃረበውን በመርዳት ከአደጋ በመሠወር ከፍተኛ የተራዳኢነት አገልግሎት ሲያበረክት ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ ቆይቶአል ።

ስለቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነትና መልአከ ምህረትነት በመጽሐፈ ሄኖክ እንዲህ ይላል ። "ሰው ባደረገው ነገር ለሕዝቡ ታዛዥ ነውና ከከበሩ መላእክት አንዱ ሚካኤል ነው ። ሄኖክ ፰ "ከመላእክት አለቆች አንዱ ቀኝ እጄን ይዞ አነሳኝ ፣ ይቅርታው ወደ ተሠወረበት ቦታ አወጣኝ ። በሰማይ ዳርቻ የተሠወሩትንም ሁሉ አሳየኝ" ሄኖክ ፳፣፴፪ ፣

አዎ ቅዱስ ሚካኤል የወደቁትን ማንሳት ልማዱ ነውና የተጐዱትን መርዳት የተቸገሩትን ፈጥኖ የሚያጽናና የተጨነቀችውንም ሕይወት ፈጥኖ በቅጽበት የሚያድን በመሆኑ ለሰዎች ባደረገው በጐነትና ፈጥኖ ደራሺነት የመላእክት አለቃ ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም የኃያሉ እግዚአብሔር ባለሟል ሲሆን ለሰዎች ግን ጠባቂ ነውና ታዛዥ ተብሏል ።

ስለዚህ ነው ዳንኤል በስቃይ ላይ በነበረበት ጊዜ ሌላ ኃይል ሊቋቋመው የማይችለውን ችግሩን ቅዱስ ሚካኤል በቅጽበት ደርሶ ስለአስወገደለትና ከጭንቁ ሁሉ ስለረዳው "ከዋነኞቹም አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ" ሲል ያደረገለትን ርዳታ የገለጸው ትንቢተ ዳንኤል ፲ ፣ ፲፫

ቅዱስ ያሬድም የቅዱስ ሚካኤልን ረዳትነትና ትህትና በምዕራፉ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል ። "ወሚካኤል አሀዱ እመላእክት እምቅዱሳን ቀደምት ፣

እስመ በዲበ ሰናይቱ ለስብእ ተአዛዚ ፣
እስመ በትህትና ረከበ ልዕልና ።
ወብዑዕ ሚካኤል ዘቦቱ ትንብልና ።
መጽአ ከመ ይዜኑ ሰናየ ዜና።"
ቅዱስ ሚካኤል ከቀደሙት ቅዱሳን መላእክት አንዱ ነው ።
በመልካም ሥራው ለሰው ታዛዥ ነውና ።
በትህትናው በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ማዕርግም አግኝቷል ።
ለሰው ልጆች መልካም ነገርን ከእግዚአብሔር ለመለን ሚካኤል ደገኛ ነው ።

ስለዚህም ለሰው ልጆች መልካም የምሥራችን ይነገር ዘንድ መጣ" ሲል ቅዱስ ሚካኤል የመላእክት አለቃ ሲሆን የሰው ልጆችን ከሚደርስባቸው ችግር ሁሉ ለመርዳት ምን ያህል እንደሚተጋ ገልጾአል ። የፍጡነ ረድኤት ቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት በብዙ መጻሕፍት ተደጋግሞ የተገለጸ ሲሆን ችግረኞችንም ከሚደርስባቸው ችግር እንደረዳ በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጾአል በተለይ በስሙ በተጻፈው ድርሳነ ሚካኤል ከፀብአ አጋንንት ፣ ከታዛዘ መቅሰፍት ፣ ከወረደ መዓት ስንት ሰዎችን እንደረዳ ተገልጾ ተጽፎአል ።

ባጠቃላይ ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች ረዳትና ርኅሩኅ መልአክ በመሆኑ የተጨነቁ ሁሉ በእግዚአብሔር ስም ወደ እርሱ ልመናቸውን ሲያቀርቡ ከእግዚአብሔር ምህረትን እየለመነ ከጭንቀታቸው ያሳርፋቸዋል ።

ቅዱስ ሚካኤል በተራዳኢነቱ ከሞት ያዳናቸው ከታዘዘ መቅሰፍት የሰወራቸው መርገሙን ወደ በረከት የለወጠላቸው እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

በዚህ ተራዳኢነቱ ማንም ሰው ሲጨነቅ ሌሊትም ሆነ ቀን በጭንቅ ተይዘው ለሚሰቃዩ ከተፍ ይልላቸዋል።

ነቢዩ ዘካርያስ ከፍተኛ ጭንቅ ይዞት እየተሰቃየ ሳለ ቅዱስ ሚካኤል ደርሶ "እነሆ አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ። ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ" ሲለው ኢያሱም ፣ ዘካርያስም በደስታ ተጽናንቶ እንደቆመ ተጽፎአል ትንቢተ ዘካርያስ ፫ ፣ ፬

በእርግጥ ከሰው ልጆች አበሳን የሚያርቅ ለንስሐ የሚጠብቅ እና የሚያበቃ የሰው ልጆች ጠበቃ በመሆኑ ሁላችንም ፍጡነ ረድኤት ቅዱስ ሚካኤል አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ እንዲለን እንማጠነዋለን እናከብረዋለን ።

በተለይም ቅዱስ ሚካኤል ሰኔ 12 የሚከበረው ታላቅ ርዳታ ያደረገበት ዕለት በመሆኑ ነው ።

ይህም እንዲህ ነው ። ከብዙ ዘመናት በፊት በአንድ አገር አንድ ሀብታም ሰው ይኖር ነበር ባጠገቡም የነበረች

ወደ ገጽ ፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ሰላም ለሁላችሁ

ሰላም በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ነው ። ሰላም የሕሊና ዕረፍት ስሜት እንዳለውም የስነ አእምሮ ሊቃውንት ይናገራሉ ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ለሰው ልጆች ሁሉ የተወሰደባቸውን ልጅነት አስመልሶ ብርሃነ መለኮቱን ተዋሕዶ ከተነሳ በኋላ አይሁድን ፈርተው በዝግ ቤት ለነበሩት ደቀ መዛሙርት በር ሳይከፍት ገብቶ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" በማለት እንደ አጽናናቸው ከዮሐንስ ወንጌል ምዕ. ፳ ፥ ፲፱ እና ፳፩ ላይ እንረዳለን ። ዛሬም ሰዎች በሚገናኙበት ጊዜ ሰላም የሚለውን ቃል መቅድም ሳያደርጉ ሐሳባቸውን አይለዋወጡም ። ጌታም ለደቀ መዛሙርቱ ወደስብከት ከመሰማራታቸው በፊት መመሪያ ሲሰጥ "በመጀመሪያ ሰላም ለዚህ ቤት በሉ" እንዳላቸው ሉቃስ በወንጌሉ ጽፏል ። ሉቃ. ፲ ፥ ፭ ።

ክርስቶስ ለ፫ ቀናት ያህል በከባድ ኃዘን ውስጥ የነበሩትን ደቀመዛሙርቱን ከትንሣኤ በኋላ በመካከላቸው ሲገኝ ሊያጽናናቸውና የምሥራቹን ሊያረጋግጥላቸው የፈለገው ሰላም በሚለው ቃል መሆኑም ቀደም ሲል ለደቀ መዛሙርቱ በቃል ያስተማረውን በተግባር መግለጹ እንደሆነ ያስረዳል ። የዚህ "ሰላም" የሚለው ቃል ምንጩ ክርስቶስ ነው ። ለዚህም የሰላም ባለቤትነቱ ከልደቱ በፊት ብዙ መቶ ዓመታት ቀደም ብለው የነበሩት ነቢያት በየዘመናቸው በትንቢታቸው በትክክል ገልጸው አስተምረውለታል ። ነቢዩ ኢሳይያስ የሰላም አለቃ በማለት ከርሱ በላይና ከርሱም በቀር የሰላም ምንጭ ሊኖር አለመቻሉን ተንብዮለታል ። ኢሳ. ፱ . ፯ ነቢዩ ኤርምያስም በበኩሉ የሰላም ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር እገባለሁ ። በማለት የሰላም ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ተናግሯል ። ኤር. ፴፬ ፥ ፳፭ ።

በሐዲስም ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው በማለት በተለያዩ ቦታ ላይ በመንፈስ እየተጠራ የምስክርነት ቃሉን አስተላልፏል ። ሮሜ. ፭ ፥ ፩ ፤ ኤፌ. ፪ ፤ ፲፬ - ፲፯ ፩ኛ ቆሮ ፲፬ ፥ ፴፫ ።

ሰላም የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን መረዳት ስለ ሰላም ያለንን አመለካከት በጽኑዕ መሠረት ላይ እንድንጥል ከማገዙም በላይ የሰላምን ጥልቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ለማጥናት በር የሚከፍትልን ነው ። መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ሰላም በውስጡ ያዘለው መልእክት ጥቂት አይደለም ። እግዚአብሔር ምሉዕ ከመሆኑ አኳያ ሰላም ውሱን ስለአልሆነ ከሦስት አቅጣጫያዊ ግዘፎች ይደመራል ለዚህም ነው በብሉይም ሆነ በሐዲስ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው ባለቤቱም ከስቅለቱ በፊት ትምህርቱን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በትንሣኤው የሞትን ሥልጣን ሽሮ "ሰላሜን እተውላችኋለሁ ብሎ እስከአረገበት ጊዜ ድረስ ደጋግሞ ያስገነዘበን ።

የሰው ልጅ በሕይወት ባለበት ዘመን ሕልውናው ከሰላም ጋር በብዙ ሺህ ድር የተሳሰረ ነው ከሰላም የተለየ የሰብለዊ ፍጡር ሕይወት የተሟላ ሊሆን አይችልም ። ለዚህም ነው ነቢያት በትንቢታቸው ሐዋርያት በትምህርታቸው ጠበብት በፍልስፍናቸው ስለ ሰላም አጥብቀው የሚናገሩት በዘመናችን የተነሱ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎችም ስለ ሰላም በሰፊው ያትታሉ አንድ የሃይማኖት መሪ "ዘዌስት እስታር" በተባለ መጽሐፍ ሰላምን አስመልክቶ ሲናገር በፍጥረተ ዓለም ለመኖር ሲባል በሚደረገው ትግል ኃይለኛው ደካማውን አጥቅቶ የመኖር ሕግ ፤ የችግሮች ሁሉ ምንጭ መሆኑ በሰው ልጆች መካከል የጦርነት የጥላቻ ፤ የጠብና የጠላትነት ምክንያት ራስን መውደድ ደበኛነት ፤ ንቀትና የሌሎችን መብት መንጠቅ የመሳሰሉትን ሁሉ የደመ ነፍሷ እንቅስቃሴዎች ደካማነት መረዳት የምንችለው የሰላምን አንፃራዊ ገጽታ ስናጤን ነው ይላል ። ገጽ 15 ሌላው በበኩሉ ስለሰላም ያለውን መንፈሳዊ አስተሳሰብ የጐመራ ተስፋ በተሸከሙ እጹብ ድንቅ ቃላት ከነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ጋር እመሳስሎ ሲገልጽ እንዲህ ይላል ። በዚህ አስደናቂ ዘመን ምድር ትለወጣለች የሰው ልጆችም በሰላምና በውበት ያጌጣሉ ። ያለመግባባት ጸብና ነፍስ መግደል ፤ ለአንድነት ፤ ለእውነትና ለስምምነት ስፍራ ይለቃሉ ። በሰዎችና በሕዝቦች በዘሮችና በሀገሮች መካከል ፍቅርና አንድነት ይመሠረታል መደጋገፍና መተባበር ተመሥርቶ የመጨረሻው ጦርነት ጨርሶ ይወገዳል ጠቅላላው ሰላም በምድር እምብርት ላይ ድንኳኑን ይዘረጋል። የተባረከው የሕይወት ዛፍ ምዕራብንና ምሥራቅን እስኪያለብስ ድረስ ይሰራጫል ። ብርቱና ደካማ ፡ ድኃና ባለፀጋ የማይግባቡ ክፍሎችና ጠላት አገሮች እንደተኩላና እንደበግ ፤ እንደፍየልና እንደነብር እንደአንበሳና እንደጥጃ ይተያዩ የነበሩት በፍጹም ፍቅር በወንድማማችነትና በትክክለኛነት አብረው ይኖራሉ ። በምድርም በሳይንስ ጠበብ እውነተኛ የተፈጥሮ ስውር ምሥጢር እውቀትና እግዚአብሔርን በማወቅ ብርሃን ትጥለቀለቃለች ። (ስም እንሰርድ ኰሽችን ገጽ ፸፫ ።)

እነዚህ ሁለቱ የሃይማኖት ሊቃውንት የቀመሩት አስተሳሰብ ምንም እንኳ በአብዛኛው ጐኑ ቀደምት ነቢያት ከተናገሩት የተለየ ባይሆንም የጥሩ ነገርን መልካምነት በሚገባ ለመረዳት የሚቻለው የመጥፎን መጥፎነት በትክክል የተገነዘበ ብቻ መሆኑን እንድናስተውል አእምሯችንን ሳይቃኘው እንደማያልፍ እምነታችን ጽኑዕ ነው ።

ሰላም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያዘለውን መሠረተ ሐሳብ ስንመረምረው በሚከተሉት ክፍሎች ሊጠቃለል ይችላል ።



፩/ በመግቢያው ላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲገናኝ ንግግሩን የጀመረው "ሰላም" በሚለው ቃል ነው ብለናል ስለዚህ ሰላም የንግግር መክፈቻ ነው ።

፪/ በርከት ያሉ ማስረጃዎችን ጠቅሰን ለማስገንዘብ እንደ ሞከርነው ሰላም በክርስቶስ የሚገኝ መንፈሳዊ ፀጋ ነው ።

፫/ በገላትያ ፭ ፥ ፳፪ እንደተገለፀው ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው

፬/ እግዚአብሔር የሰላም ባለቤት ነው ስንል ሰላምን ለግሉ ያስቀራል ማለት አይደለም የራሱን ሰላም በሕጉና በፈቃዱ ጐዳና ለሚመላለሱና በቅድስናው አደባባይ ለሚከትሙ ወዳጆቹ ይሰጣል ። ለዚህም አባባል መነሻቸው "በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ ። የሚለው የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢትና የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና ሐሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል የሚለው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ነው ኢሳ. ፳፮ ፥ ፫ ፥ ፊልጵ ፬ ፥ ፯ በዚህም መሠረት እግዚአብሔር የራሱን ሰላም ለሚከተሉት እንደሚሰጥ እንረዳለን ።

፭/ ሰላም አማኞች እንዲኖሩበት እንደግዴታ የተሰጠ ነው ። ምንአልባት ሰላምን በትእዛዝና በግዴታ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነና ጽንሰ ሐሳቡንም የተሟላ ሊያደርገው እንደማይችል የምንገምት ጥቂቶች እንሆንም ይሆናል ። የሰላም መንፈሳዊ ትርጉምም ይህን ከመረዳት ላይ ነው ታዛዥነትን በተግባር መግለጽ የክርስቲያኖች ሁሉ የመመዘኛ ነጥብ ነው ።

ይህ ለእውነተኛ ክርስቲያኖች አስቸጋሪ አይደለም አንድ ክርስቲያን ትእዛዝን በፈጸመ ቁጥር የሚሰማው ደስታ እጥፍ ይጨምራል ። ያኔም ሰላም ከሰውነቱ ጋር ይዋሐዳል ። ስለዚህ ከራሱ ግልብ አመለካከትና ወልጋዳ አስተሳሰብ ተላቆ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚመራ ክርስቲያን ትእዛዝን መፈጸም ከባድ አይደለም ። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ብዙ ትእዛዛት አሉ። ከነዚህ ትእዛዛት አንዱን የጣሰም ሁሉንም እንደጣሰ መ/ ቅዱስ ይናገራል ። በዚህ መሠረት በሰላም የማይኖር ክርስቲያን ትእዛዛትን በመላ እንደሻረ መረዳት ተገቢ ነው ። በሰላም መኖር ለክርስቲያኖች ትእዛዝ እንደሆነ ያስታወቁን ታላላቆቹ ሐዋርያት ጳውሎስና ጴጥሮስ ናቸው ። ጳውሎስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ብሎ ሲያዝ ጴጥሮስም በበኩሉ ሕይወትን ሊወድና መልካሞቹን ቀናት ለማየት የሚፈልግ ሰው ሰላምን ይሻ ይከተለውም በማለት ትእዛዙን ከሕይወት ጋር አያይዞ ያብራራል ። ሮሜ. ፲፪ ፥ ፲፰ ፤ ፩ኛ ጴጥ. ፫ ፥ ፲፩ ።

፮/ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም ናት በማለት የጻፈውን ስንመለከት ደግሞ ሰላም ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ተያይዞ እናገኘዋለን ። ስለዚህ ሰላም ያለጥርጥር የእግዚአብሔር መንግሥት ነው ። ሮሜ ፥ ፲፬ ፥ ፲፯ ። እንግዲህ ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ ለሚኖር ሁሉ ሰላም አትሰጥም ። ለክፉዎች ሰላም የላቸውም የሚለውን የነቢዩ ኢሳይያስን ትምህርት ስንመለከትም እነዚህ ክፉዎች ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ መሆናቸውን እንገነዘባለን ኢሳ. ፵፰ ፥ ፳፪ ፤ ፶፯ ፥ ፳፩ ፤

፯/ ሰላም የተሟላ የሚሆነው ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ነው ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ የሰላም መሠረት የሆነው ፍቅር ለዘለዓለም ፀንቶ እንደሚኖር ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በግልጽ ያስረዳል ። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፲፫ ። ነቢዩ ኢሳይያስም የሰላም ፍጻሜ የለውም ሲል የሰላምን ዘለዓለማዊነትና ፍጹምነት በማያሻማ አነጋገር ይገልጽልናል ኢሳ.፱.፯ እንደዚሁም ይኸው ነቢይ እንደተናገረው እጅግ ተጻራሪ የሆኑ ኃይሎች ሁሉ አብረው እስከመኖር ድረስ የእግዚአብሔር ሰላም ይነግሣል ኢሳ. ፲፩ ።

እስካሁን ድረስ ለመግለጽ የተሞከረው ሰላም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን አመለካከት ሲሆን ሌሎችም መጻሕፍት የሚሰጡት ሐሳብ ከዚህ የተለየ አይደለም ። እንዲያውም ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ የሚስማሙበት ሐሳብ ሰላም ነው ። በዚህ መሠረት ከተለያየ አቅጣጫም ቢሆን ሰላምን የሃይማኖት ሰዎችም ሆኑ ኢአማንያን በጥብቅ ይፈልጉታል ።

ዛሬ ዓለም በጠቅላላው ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ሰላም ሰላም እያለ እየጮኸ ነው። መንግሥታት ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተቋሞችና የሃይማኖት ድርጅቶች የዘወትር ጭንቀታቸው የሰላም ጥያቄ ሆኗል ። በተለይ በጦር መሣሪያዎች በኩል የሚደረገው ፈጣን እሽቅድምድም ዓለምን ከሕሊና ጭንቀት ላይ ጥሏታል ። ሣይንስና ጥበብ እያደገ በሄደ ቁጥር ውጤቱ በመጀመሪያ የሚታየው በጦር መሣሪያዎች ላይ ሆኗል ። የአንደኛው ዓለም አንቀሳቃሽ ኃይሎች ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት የጦር መሣሪያ ቅነሳ ለማድረግ ከአንድ እስከ ሦስት ጊዜ ያህል መስማማታቸው ይታወሳል ። ሁሉም ሰላም ፈላጊዎች መሆናቸውን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለዓለም ያስተጋባሉ ። ነገር ግን በአንድ በኩል የጦር መሣሪያ ቅነሳው ውል ሲፈረም በሌላ በኩል ደግሞ የጦር ጠበብቶቻቸው አዲስ የጦር መሣሪያ ዲዛይን (ሞዴል) አውጥተው ያድራሉ ከዓመት ወደ ዓመት እጅግ በጣም የተራቀቁ የጦር መሣሪያዎች ሲሠሩ እንጂ ሲቀነሱ ዓይናችን አላየም በዚህም መሠረት ዓለም በጠቅላላው መሸ ነጋ ሳይል አዘውትሮ የሚጮህለት ሰላም ፈለጉ እየጠፋ ዱካው እየራቀ ከመሄድ በስተቀር ጨረፍታው እንኳ ሊታይ አልቻለም ። እ.ኤ.አ. በአለፈው ዓመት መጨረሻ አካባቢ ሰላምን በማስመልከት በተለያዩ ቦታዎች ከፍተኛ ሰብሰባዎች ተደርገዋል ። ከ ፶፫ ሀገሮች የተውጣጡ ፪፻ የሚሆኑ ብሔራውያን የሰላም ልዑካን ተወካዮች የብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች ፲ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የታወቁ የፖለቲካና የሃይማኖት ሰዎች እንዲሁም የፓ

ተከታዩን በገጽ ፲፫ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# የሳምባ ነቀርሳን እንዴት መከላከል ይቻላል?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በዓለም ከታወቁት ተላላፊ በሽታዎች አንዱ ነው ። በሀገራችንም በተላላፊነቱ ሁለተኛ ደረጃን የያዘ መሆኑ ታውቋል ። ለበሽታው መነሻ ምክንያት የሚሆኑት ጀርሞች አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠቁት ሳንባን ሲሆን ነገር ግን ሌሎችንም የሰውነት ክፍሎች በመበከል ከበድ ያለ ጉዳትን ሊያስከትሉ ይችላሉ ።

ጀርሞች ወደ ሰውነት ሊገቡ የሚችሉት በሁለት መንገዶች ነው ። ይኸውም ከሰው ወደ ሰው ወይም ከከብት ወደ ሰው በመተላለፍ ይሆናል ። በሽታው ከከብት ወደ ሰው የሚተላለፈው ያልተጣራ ወይም ያልተፈላ ወተትን በመጠጣት ሲሆን በይበልጥ የሚያጠቃው ሕፃናትን ነው ። ካልተፈላ ወይም ካልተጣራ ወተት ብዙ ዓይነት በሽታዎች ሊተላለፉ ይችላሉ ይሁን እንጅ የሳንባ ነቀርሳ ሊተላለፍ የሚችለው ከብቷ በበሽታው የተበከለች ከሆነች ነው ። ከከብት የሚተላለፉት ጀርሞች ብዙውን ጊዜ የሚያጠቁት በአንገት ላይና በአንጀት ውስጥ የሚገኙ እጢዎችንና አጥንትን ነው ። በሽታው አንጀትን ከበከለ የሚያሳያቸው ምልክቶች ከምግብ በኋላ የመንፋት ስሜት ቁርጠት ተቅማጥ ወይም ድርቀት ሊኖር ይችላል፤ አንዳንዴም ከእምብርት በታች ሊዳሰስ የሚችል እብጠት ሊፈጥር ይችላል ።

እንግዲህ ከከብት ወደ ሰው የሚተላለፉት ጀርሞች ከላይ የተጠቀሱትን የአካል ክፍሎች ሲበክሉ ከሰው ወደሰው የሚተላለፉት ጀርሞች ደግሞ የሚያጠቁት ሳንባን ብቻ ነው ። በሽታው ከተበከለው ሰው ወደ ጤናማው ሊጋባ የሚችለው በትንፋሽ በማነጠስ እንዲሁም በመሳል ይሆናል ። ይህ በቀጥታ ወዲያውኑ ሊተላለፍ የሚችልበት መንገድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ በአክታ ይተላለፋል ። የሳንባ ነቀርሳ ጀርሞች በደረቅ ቦታ በአየር ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት ስለሚችሉ ጤናማውን በመበከል ይጐዱታል ።

የሳንባ ነቀርሳ እንደያዘው አንድ ሰው ወዲያውኑ ለማወቅ አይችልም ። ምክንያቱም በሽታው ሲይዝ ወዲያውኑ በራጅ ካልሆነ በስተቀር ለሰውየው ምንም ዓይነት ምልክት ስለማያሳይ ነው ። ይሁን እንጅ ቆይቶ በሽታው የሚከተሉትን ምልክቶች ያሳያል የምግብ ፍላጐት ማነስ ፣ የሰውነት ክብደት መቀነስ ድካም ፣ የሌሊት ላብ ፣ መጠነኛ ትኩሳት ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ሳልና አልፎ ኋልፎ የደረት ውጋት ይሆናሉ ። በመጀመሪያ የሚያስለው ደረቅ ሳል ይሆናል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን አክታ ያለው ሳል ይስላል ። አክታውም ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል ። አንዳንዴም የመተንፈስ ችግር ሊኖር ይችላል ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምልክቶች ይሁኑ እንጅ በሽታው በተገቢው ምርመራ ተመርምሮ እስካልተረጋገጠ ድረስ ሌሎችም በሽታዎች ይህንኑ የመሰሉ ምልክቶችን የሚያሳዩ ስላሉ በምልክቶች ብቻ በሽታው ይዞኛል ወይም አልያዘኝም ለማለት አያስደፍርም ። ይሁን እንጅ ምልክቶቹን ማወቁ በቶሎ ለመመርመር ያዘጋጃል ።

ይህ በሽታ ከነጮች ይልቅ ጥቁሮችን ያጠቃል ። አብዛኛውን ጊዜ ከባድ ጉዳት ሊያስከትልና በቀላሉ ሊዛመት የሚችለው በተጣበበና ንጽህናው ባልተጠበቀ ቤት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች የኑሮ ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ በሆነ የአልኮሆል መጠጥ በሚያበዙ ፣ የስኳር በሽታ በያዛቸው በሕፃናትና እንዲሁም በአረጁ ሰዎች ላይ ነው ። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት በሽታውን የሚቋቋሙበት ኃይል ስለሌላቸው በቀላሉ ሊጠቁ ስለሚችሉ ነው ።

የበሽታው ሁኔታ ባጭሩ ከላይ እንደ ተገለጸው ሲሆን ለመከላከል የሚረዱ ዘዴዎችም የሚከተሉት ናቸው ።

፩ አንድ ሰው በበሽታው ከመያዙ በፊት መከላከያ ክትባት መውሰድ

፪ በበሽታው ከተያዙ በኋላ በተለየ ሁኔታ ሕክምናውን ማግኘት

፫ በሽተኛው በሚስል ወይም በሚያስነጥስ ጊዜ አፉን በመሃረብ ቢሸፍን ጀርሞች ከርሱ አልፈው ወደ ሌላ ለመዛመት እድል አያገኙም ።

፬ አክታውን በማንኛውም ቦታ በመትፋት ፋንታ በአንድ የተወሰነ ዕቃ በማጠራቀም መቅበር ወይም ማቃጠል ጀርሞቹ በተወሰነ ቦታ እንዲቀሩ ያደርጋል ።

፭ በሽተኛው ለብቻው በሆነ በደንብ በተናፈሰና ንጽሕናው በተጠበቀ ክፍል ውስጥ እንዲተኛ ማድረግ ።

፮ በበሽታው በቀላሉ ሊጠቁ የሚችሉትን እንደ ሕፃናት ወይም ያረጁ ሰዎችን በሽታው ከያዛቸው ሰዎች እንዳይቀርቡ ማድረግ ።

፯ ማንኛውንም ወተት ማፍላት ያልተጣራ ወይም ያልፈላ ወተት አለመጠጣት ።

፰ በተቻለ መጠን በአንድ ቤት ውስጥ በጣም በዝቶና ተጣቦ መኖርን መቀነስና የመሳሰሉት ናቸው ።

በሽታው እንዳይስፋፋና እንዳይሰራጭ ለማድረግ ከጤናማው ሰው ይልቅ የበሽተኛው ጥንቃቄ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ተማሪ ነርስ ልዕልት ረታ

# ደብዳቤዎች.....

ከገጽ ፩ የዞረ

ው የሚናገረውን አምኖ መቀበል ነው።

፱ኛ/ ሟቹ ሕፃን የክርስቲያን ልጅ ከሆነ ቢጠመቅም ባይጠመቅም የክርስቲያን ልጆች በሚቀበሩበት በዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ሊቀበር ይችላል ።

በፍትሐ ነገሥት አንቀጸ ሙታን ላይ ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ሕፃን ከሕፃን መቃብር ይቀበር ተብሎ ተጽፏልና ።



# ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያን

“ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው አንደኛው ምእመናንና ካህናት ለጸሎት ፣ ለስግደት ፣ ለምስጋና ፣ ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል የሚሰበሰቡባት ፤ በጸሎትና በቅብዓተ ሜሮን የከበረች ልዩ ሕንፃ (ቤት) ማለት ስትሆን ሁለተኛው በእግዚአብሔር ስም አምነው የክርስቶስን አዳኝነት ተቀብለው የተጠመቁ ምእመናን ሁሉ በጠቅላላ ቤተ ክርስቲያን እየተባሉ ይጠራሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ተከታይ ማለት ሲሆን መጀመሪያ አማኞች ክርስቲያን ተብለው የተጠሩት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፵፮ ዓ.ም. ነው በሐዋርያት ስብከት ተስበው በክርስቶስ ስም ያመኑት ፰ሺ ምእመናን እንደ አንድ ልብ መካሪ ፤ እንደአንድ ቃል ተናጋሪ ፤ ሆነው እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር ፤ ነገር ግን የክርስትና እምነት ተቃዋሚዎች ተነሥተው ለክርስትና እምነት ከፍ ያለ ፍቅር የነበረውን ፤ ለማስተማርና ለማስረዳት መንፈሳዊ ጥበብ የተመላውን እስጢፋኖስን ሲገድሉት ሁሉም አማንያን በየፊናቸው ተበታተኑ ።

ከተበታተኑም በኋላ እንደገና አንዳንድ እያሉ በአንጾኪያ መሰብሰብ ጀምረዋል ። በዚያን ጊዜ የመጀመሪያዎቹ አርድእት በዚሁ ቦታ በአንጾኪያ ክርስቲያን የሚለውን ስያሜ አግኝተዋል የሐ. ሥራ ምዕ. ፲፩.፳፮/

ከክርስትና በፊት ግን በእግዚአብሔር ስም ያመኑ ሁሉ በኅብረት ተሰብስበው አምላካቸውን የሚያመሰግኑባቸውና የአምልኮት ሥነ ሥርዓት የሚፈጽሙባቸው ደብተራ ኦሪት ፤ ቤተ መቅደስና ቤተ ምኩራብ የሚባሉ ነበሩ ደብተራ ኦሪት ድንኳን ናት ፤ የነበረችውም ቤተ መቅደስና ቤተ ምኩራብ ከመመሥረታቸው በፊት ከሙሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ዳዊት ዘመን ነው ።

እስራኤል በግብጻውያን ቀንበር ተይዘው እየተጨነቁና እየተሰቃዩ ፬፻፴ ዘመን ሙሉ ከኖሩ በኋላ እግዚአብሔር ኃዘናቸውን ሰምቶ ጭንቀታቸውን ተመልክቶ በሙሴ መሪነት ከባርነት ቀንበር አወጣቸው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ እግዚአብሔር በደብረ ሲና ለሙሴ ደብተራ ኦሪትን እንዲሠራ ምሳሌዋን አሳይቶታል ወዲያው ከእስራኤል ሕዝብ መካከል በጥበብ የተራቀቁትን ባስልኤልንና ኤልያብን መረጠና ደብተራ ኦሪትን እንዲሠሩ አደረገ ።

በደብተራ ኦሪትም የመሥዋዕት የምስጋና የጸሎት የስግደት የመሳሰሉትም አገልግሎቶች ማቅረቢያ የንዋያተ ቅድሳት ማስቀመጫ ተዘጋጅተው ተወርተው ነበር ፤ ስለደብተራ ኦሪት ይዞታ ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቅሶ ሲናገር በእርሷም ቅድስት በምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛው የመስዋዕቱም ኅብስት ነበረባት ፤ ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች ፤ በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለተኛዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርሷም ውስጥ መና ያለበት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ ፤ ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ ካህናት አገልግሎታቸውን ዘወትር እየፈጸሙ በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል ፊተኛይቱም ድንኳን በዚህ ቁማ ሳለች ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው” ብሏል ዕብ. ፱ ፡ ፩-፲ ።

በደብተራ ኦሪት የሚፈጸሙት አገልግሎቶች እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ ሲፈጸሙ ቆይተዋል ዳዊት በዘመኑ ቤተ መቅደስን ለማነፅ አስቦ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቆ ነበር ፤ ነገር ግን ልጁ ሰሎሞን እንጂ እርሱ ቤተ መቅደስን ለመሥራት የማይችል መሆኑን ነገረው። የሐ.ሥራ. ፯ ፡ ፵፯ ።

ዳዊት ከሞተ በኋላ ሰሎሞን ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም ቤት እሠራ ዘንድ አስባለሁ አለ እግዚአብሔርም መልካምና ቅን አሳቡን ተመልክቶ እንዲሠራ ስለፈቀደለት ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ታቦተ ጽዮንን ከደብተራ ኦሪት ወደቤተ መቅደስ አስገብቶ በደብተራ ኦሪት ይፈጸም የነበረው አገልግሎት ሁሉ በቤተ መቅደስ ይፈጸም ጀመር ። ፩ኛ ነገ. ፭.፭ ፡ ፰. ፩-፭ ።

ይህም ቤተ መቅደስ እስከ ዘመነ ክርስቶስ ድረስ የአገልግሎት ሥርዓት ሲከናወንበት ኑሯል ትን ዳን. ፱.፳፭ ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ቀስ በቀስ አድጐ ሰላሳ ዓመት ሲሆነው በማየ ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ተጠምቆም አልዋለም አላደረም ወዲያውኑ ወደገዳም ሄዶ ፵ ቀንና ሌሊት ጾመ በጾሙም መጨረሻ ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑትን ደቀ መዛሙርቱን መርጦ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሮ አሠልጥኖ ሲያበቃ የሰውን ልጅ ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማውጣት ሲል በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ሞትን በሞቱ አሸንፎ ተነሥቶ ከደቀ መዛሙርቱና ከሌሎችም ተከታዮቹ ጋር አብሮ እየበላና እየጠጣ ሲያስተምር ቆይቶ በ፵ ቀኑ ወደ ሰማይ አረገ ።

ነገር ግን ከማረጉ ፊት ቤተ ክርስቲያን እንደምትመሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ ሲነግረው የዩና ልጅ ስምዖን ሆይ ! አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም ብሎ ነግሮት ነበር ። ማቴ. ፲፮ ፡ ፲፰ ።

በዚሁ መሠረት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሐዋርያት ይህንን ዓለም በዕጣ ተከፋፍለው ሲያስተምሩ አማንያን እየበዙ ይሄዱ ጀመር ፤ ነገር ግን የሚጸልዩበት የሚሰግዱበት ምስጋና የሚያቀርቡበት ምሥጢረ ቁርባንም



www.ethiopianorthodox.org

የሚፈጽሙበት ቤተ ክርስቲያን አልተሠራላቸውም ነበርና የሚጸልዩት የሚሰግዱት የሚያመሰግኑት ምሥጢረ ቁርባንም የሚፈጽሙት በእሪቱ ቤተ መቅደስ ነበር (ሉቃስ. ፳፬.፶፫) የሐ. ሥራ ፪.፵፮) በዚያው ዘመን ከደቀ መዛሙርቱ ጳውሎስና በርናባስ ፊልጵስዩስ በምትባል አገር ወንጌልን በሰፊው ሲያስተምሩ፥ ብዙ ሰዎች የክርስትና እምነትን ተቀብለው በክርስቶስ ስም ተጠመቁ የክርስትና እምነትን የተቀበሉት አማንያንም ጳውሎስንና በርናባስን የጸሎት ቤት ሥሩልን አሏቸው እነርሱም የፊልጵስዩስ ሰዎች የጸሎት ቤት ሥሩልን ብለው ጠየቁን እንዴት እናድርግ ብለው ኢየሩሳሌም ለሚገኙት ለጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩባቸው በዚህ ጊዜ እነርሱም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንምን ለመሥራት እንደማይቻሉ ገልጠው ከሕዝቡ ጋር ሱባኤ በመግባት እግዚአብሔርን በጸሎት እንዲጠይቁ አሳሰቧቸው ። ጳውሎስና በርናባስም እነጴጥሮስ እንደ ነገሯቸው ከሕዝቡ ጋር ሆነው በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ በሱባኤያቸው መጨረሻ ላይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ከያሉበት በደመና ጠቅሶ ወደፊልጵስዩስ ወሰዳቸው በዚያም ጳውሎስና በርናባስ ነበሩና እነርሱን ይህች ዕለት በእናቱ ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን እንድትታነፅ የፈቀድሁባት ዕለት ናት ብሎ ወዲያውኑ ከፊልጵስዩስ ወደ ምሥራቅ ክፍል ወሰዳቸው ።

በዚያም የቤተ ክርስቲያንን አሠራር ለክቶ እንዲሠሩ ሐዋርያትን አዘዛቸው እነርሱም ዕለቱን ሳይውሉና ሳያድሩ የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ መሥራት ጀምረዋል ከእነርሱ ጋር ኃይለ እግዚአብሔር አብሮ ይሠራ ስለነበር ቀን እነርሱና አማንያኑ ሲሠሩት የዋሉት ሕንፃ በጧት ሲመለከቱት ጨምሮ ይገኝ ነበር ይባላል ።

ይህችን የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሐዋርያት ያነጿት ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ በ፳፱ኛው ዓመት ከልደቱ በኋላ ፷፪ኛው ዓመት ነው ሐዋርያት ሰኔ ሃያ ቀን ሠርተው ጨርሰው በዚሁ ወር ፳፩ ቀን ቅዳሴ ቤቱን አክብረው ታቦተ ማርያምን አስገብተው ቀድሰው ቆርበው ምእመናንንም አቁርበዋል ። ይህንንም ሰኔ ፳፩ ቀን እንዲነበብ ከተጻፈው ስንክሳር ተመልክቶ ለመረዳት ይቻላል ።

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች የደብተራ ኦሪት ፣ የቤተ መቅደስና የቤተ ምኩራብ ምሳሌነት ሁሉ በእርሷ የተፈጸመባት ናት ።

ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ስብ አጢሱ ደም አፍስሱ የሚለው ኦሪታዊ ልማድ ሁሉ አልፎ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ የሚለው አዲስ ሥርዓተ ቁርባን ተተክቷል ፤ አሠርቱ ቃላተ ኦሪትም በስድስቱ ቃላተ ወንጌል ተፈጽመዋል በዚህ ዓለም ላይ የነበረው ልዩ ልዩ እምልልኮ ባዕድም ተሽሮ ክርስቲያናዊ እምነት በየአቅጣጫው ተስፋፍቷል ቤተ ክርስቲያንም የዚህ ሁሉ መደምደሚያና መፈጸሚያ ሆናለች ።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር የሌለበት ቦታ ባይገኝምና በዓለም ሙሉ መሆኑ ቢታወቅም በቤት ወይም በሌላ ቦታ ሆነው ከሚጸልዩት ጸሎት ይልቅ በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ የሚጸልዩት ጸሎት የበለጠ ዋጋን የሚያስጥ በመሆኑ ማነኛውም አማኝ በቤተ ክርስቲያን እየተገኘ ጸሎቱንና ምስጋናውን ስግደቱንና የመሰለውንም አገልግሎት ማቅረብ ይገባዋል ።

ቁ. ል ነ ወርቅ በዛብህ

# ቅዱስ ሚካኤል....

ከ፻ኛው ገጽ የዞረ

አንዲት ድሀ ሴት በቅርቡ ባሏ ሞቶባት ወዲያው ልጅ ወለደች ይህ ዓመጸኛ ሀብታም ሰው በሰዎች ላይ ግፍ የሚሠራ በጐረቤቱ የሚኖሩ ድሆችን የሚበድል በተለይ ይህችን እመጫት ሴት ከነባሏ የሚበድል ነበር ። በዚህ ምክንያት ይህ ሕፃን አመጸኛውን ሀብታም እንደሚወርስ ንግርት ይሰማ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሀብታሙ ሕፃኑን በልዩ ልዩ ዘዴ ከእናቱ ወሰደና በሳጥን አሽጐ በባህር ላይ ጣለው እግዚአብሔር ግን ይህንን ሕፃን በአንድ የበግ እረኛ አማካይነት አዳነው ያ የበግ እረኛ በጐቹን ውሀ ሲያጠጣ ሕፃኑን ከነሣጥኑ ሲንሳፈፍ ስለአገኘው ሕፃኑ በበግ እረኛው ቤት አድጐ የበግ እረኛውን እያገለገለ ሳለ አመጸኛው ሀብታም በንግድ ሥራ ምክንያት ያ ሕፃን ከሚያድግበት ቤት ስለደረሰ አሁንም የእግዚአብሔርን አዳኝነትና የቅዱስ ሚካኤልን ተራዳኢነት በመጋፋት ሕፃኑን የሞት ደብዳቤ አስይዞ ወደሀገሩ ላከው ። እግዚአብሔርም የተገፉትን ማዳን ልማዱ ነውና እንደገና በመልእክተኛው በቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የሞቱን ደብዳቤ ወደ ሕይወት ለወጠው ። ከዚህም በላይ ያ ሕፃን ልጅ የሀብታሙን ሴት ልጅ እንዲያገባና ሀብቱን እንዲወርስ እግዚአብሔር በመልእክተኛው በቅዱስ ሚካኤል አዘጋጀለት ሀብታሙ ከሄደበት ቢመለስ ሁለት ጊዜ እንዲሞት የተመኘለትና ሞት ፈርዶበት የሞተ የመሰለው ሕፃን ሀብቱን ወርሶ ልጁን አግብቶ በታላቅ ደስታና ክብር ሆኖ አገኘው ። በዚህ ጊዜ ደንግጦ ሞተ ። የአመጸኛው ባለጸጋ ሚስትም በባሏ ሞት ደንግጣ ወዲያው ተቀሰፈች ። ሁለቱም በአንድ ጉድጓድ ገቡ ። ከዚህ ላይ ነው ቅዱስ ሚካኤል የሰዎች ታዛዥ ሆኖ ምህረትን ከእግዚአብሔር ይዞ የተገፉትን ሊረዳ ተጋፊዎችን ሊቃወም ይገሰግሣል ተብሎ የተነገረው ።

እግዚአብሔር ሊረዳው የፈለገውን የሰው ሀሳብ ሊያግደው አይችልም እንደተባለው እግዚአብሔር በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ሊረዳው ያሰበውን ባህራንን የባለጸጋው ሀሳብ ሊያጠፋው ከቶ አልቻለም ። ጠባቂውና ረዳቱ ተራዳኢው ቅዱስ ሚካኤል ነውና ። ያ ግፈኛ ባለጸጋ ሀብቱ የተሰጠው የሌላቸውን እንዲረዳበት መሆ

ተከታዩን በገጽ ፲፯ ይመልከቱ



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## ፫ኛ አመዛዛኝ ድርሰት

ከተግባር ወይም ከድርጊት ተነስቶ በአእምሮ የተጸነሰ ጉልህ አሳብ ከውስጣዊ ስሜት እየፈለቀ በብርዕ እንደብት የሚወለድ ጉሥአተ ልብ ጥቅምና ጉዳቱ ብርቱና ደካማ ይዘቱ ተመዛዝኖ አንዱን ከሌላው ጋር ለማወዳደር ተቀናብሮ የሚቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው ።

ለማስረጃ ያህል የሚከተለውን ድርሰት እንመርምር ፤

ርእስ፦

## የክብር ልዕልና ማግኘት የሚቻለው በኃይል ወይስ በትህትና ?

"ግርማው በሚያስፈራ በሸለቆ መሐል
እንደሊማሊሞ ጥላሞት በሚጥል
ከላይ ገደል ሆኖ ከበታችም ገደል
ዕዝራ በራእዩ ያየትን የምታህል
አንዲት ጠባብ መንገድ ጭራ የምትመስል
አቋርጣ የምታልፍ መሐሉን በመከፈል
ነበረች" ይላሉ በጥንታዊት ቻይና
አስደናቂ አባባል አስገራሚ ዜና ።
በቀንዳቸው መሾል እጅግ የሚያስፈሩ
ሁለት አደገኞች የፍየል አውራዎች ቀን የተሰማሩ
ለምለም ሣር ለማግኘት ቅጠል ሊማርሩ
በዚያች ጠባብ መንገድ ፊት ለፊት ሲያመሩ
ድንገት ተገናኝተው በኃይል ተፈራሩ
መተላለፊያ አጥተው ስለተቸገሩ
ያልታሰበ አደጋ ጦርነት ፈጠሩ
ምርጫው ውጊያ ሆኖ መጓጓን ጀመሩ
በኋላ እግሮቻቸው እያፈገፈጉ
ድርብ ኃይል አግኝተው ጠንክረው ተዋጉ ።
ዳሩ ግን ዘግይቶ የተገኘው ብልሃት
ድል ለሁለታቸው እንደማትሆን አውቀው ውጤቱን
ተረዱት ።
ስለዚህ አንደኛው ትህትና ለመሥራት
ጉልበቱን ዝቅ አርጎ በርከክ በማለት
ውጊያውን አቁሞ መሬት ሲተኛለት
ሌላው አውራ ፍየል ዘሎት በመራመድ
ለመትረፍ ችለዋል ከአደገኛ ወጥመድ"።
የምሳሌው ፍሬ ሐሳብ (ትርጉም)
ፈተና ሲገጥመው ከእልኸኞች ጋራ
ሰውም እንደዚሁ ትህትና ቢሠራ
ለመትረፍ ይችላል ካሣር ከመከራ ።
ልዕልናም ያገኛል ከፍተኛ ሥፍራ
በእልህ አይደለም ወይ ገና ከጅምሩ
ሰው ከእግዚአብሔር ጋራ ሲታገል መኖሩ ።
ከገነት ተሰዶ ምድረ ፋይድ ቢወርድ ንፍር ውሃ ዘንሞበት ከምድር ቢወገድ መሬት ስትከዳው ተራሮች ሲናዱ
በእሳተ ገሞራ መቃጠል መንደዱ.
ሰባት ጊዜ ቢያጥር የዕድሜ ገመዱ.
በአባርቸነፈር ድባቅ መምታቱ
ሊገታው አልቻለም ሰውን ከክፋቱ
ብርቱ እልህ አለበት ሰው በሰውነቱ
ኃይል አይበግረውም እስጊዜ ሞቱ
ቅጣት አይገታውም አትልፉ በከንቱ ።
ትህትናን እንደልብስ ከተጎናጸፈ
ሰው መልአክ ይሆናል በክንፍ የታቀፈ
ጠላትም ቢገፋው እስከ መጨረሻው
በቀላል አይወድቅም ትሕትና ያለው ሰው ።
ግን በኃይል ሥራ በእልህ የታበዩ
በአጭር ጊዜ ወድቀው በዓለም ላይ ሳይቆዩ ።
ተረስተው ቀርተዋል ታይተው እንዳልታዩ ።
ስለዚህ ከመልአክ በክብር እንዳታንሱ
ልዕልናን ለማግኘት ትሕትናን ልበሱ
ትሕትናን ልበሱ በዕውነት ንቁ ቁሙ
ክርስቶስን መምሰል ይኸው ነው ትርጉሙ ።
ዘለዓለማዊ የሆነ የማያቋርጥ ሰላም
መገኘት የሚችለው በትሑት ሰው ዘንድ ነው ።
(ኢሳ. ፶፩፥፳፩)
ከእናንተ መካከል የበላይ መሆንን የሚወድ
ቢኖር የእናንተ አገልጋይ ይሁን ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ይዋረዳል ፤
ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ከፍ ይላል ።
(ማቴ. ፳፫፥፲፩-፲፪)

ቁ/መክብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

**ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የ ..ሰጡበት ፤ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።**




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቊጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37

አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት
ምን እንርዳዎ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን እያልኩ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ፤

፩ኛ/ እኔ ከዲቁና ወደ ቅስና ለመሸጋገርና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በቅን ለማገልገል ፍጹም ሀሳብና ፍላጐት ነበረኝ፡ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን ያለው ጭቅጭቅ እና ቅንአት ምቀኝነት በጣም እየተስፋፋ በመሄዱ ያለኝ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እየቀነሰ ስለሄደ ምን ማድረግ ይሻለኛል?

፪ኛ/ ወደ ቅስና ማዕረግ ለመድረስ በጋብቻ ወይም በምንኩስና የተወሰነ ስለሆነ እኔም በዚሁ መሠረት በሕግ አግብቼ ለመኖር አስቤ ነበር ። ዳሩ ግን ለእኔ የምትሆን የትዳር ጓደኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆነች ለቅስና የምትሆን ለመፈለግ ብሞክርም ለጊዜው መንፈሳውያት ይመስሉና ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተቀይረው አያቸዋለሁ አሁን ግን የማግባቱ ሙከራ በጣም እየቀዘቀዘ ሄዷል ። ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻለኛል?

፫ኛ/ በጋብቻ የጣት ቀለበት የጆሮ ፤ የአንገት ሀብል ፤ ቦርሳ እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶች ካላሟላ ማግባት እንደማይቻል እሙን ነው ይህ ያለአግባብ የሚባክን ገንዘብ የሚጋቡት ኑሮአቸውን ቢያሻሽሉበት የተሻለ ስለሆነ በዚሁ በመጽሔታችሁ ለሴቶች እህቶቼ ምክር ትለግሷቸው ዘንድ ጥያቄ ዬን ለቀርባለሁ ።

ሊቀ ዲያቆን አወቀ ፍትጉ
ከደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን

ሊቀ ዲያቆን አወቀ ፍትጉ የላኩልን ጥያቄዎች ደርሰውን ተመልክተናቸዋል ። አንደኛው ጥያቄ በዲቁና የሚያገለግሉዋትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ወደፊትም በቅስና ለማገልገል ማሰዎንና ለዚህ አገልግሎት እንቅፋት የሆኑብዎትን ነገሮች ዘርዝረው የገለጹት ነው ።

መቼም ለመልካም ነገር እንቅፋት የማይታጣ በመሆኑ እርስዎ በመንፈሳዊ አንዋዋር ለመኖርና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም በቅንነት ለማገልገል አስበው ሳለ ሆነ ብለው እንቅፋት የሚሆኑ ካጋጠሙዎ በትዕግሥት ማሳለፍና ወደ እግዚአብሔርም በመጸለይ በመንፈሳዊ ሥርዓት ማሸነፍ አለብዎት እንጂ ተበሳጭተው ለመተው ማሰብ የለብዎትም ።

መጽሐፍ "እስከመጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል ማቴ. ፲፥፳፪" ስለሚል እርስዎም እስከ መጨረሻው ድረስ መታገስ አለብዎት እንጂ በቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ በሚታዩት ጭቅጭቆች ተስፋ ቆርጠው ከመንፈሳዊ ዓላማዎ ፈቀቅ ሊሉ ከቶ አይገባም ።

በየትኛውም የሥራ መስክ ቢሆን ካልታገሱ እንቅፋት አይታጣምና በያዙት ላይ መታገስ ነው ፤ ትልቁ ነገር ። ትዕግሥት መራራ ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው ተብሏልና ።

በቤተ ክርስቲያናችን ጭቅጭቅ ፤ ቅንአትና ምቀኝነት በአንዳንድ ቦታዎች እየተስፋፋ በመሄዱ ይህንን ጉዳይ ማስታገስ የሚቻለው በፍቅር በትዕግሥትና በየዋሀት ስለሆነ ድል ማድረግ የሚችሉት በፍቅር መሆኑን አውቀው እስከመጨረሻው ይታገሱ ።

በመሠረቱ ግን ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን እርሷም የሚገባት ለዓለም ሰላምን ማወጅ ነበር ። ዛሬ ግን በሁሉም ባይሆንም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚታየው በቤተ ክሮስቲያን አገልጋዮች መካከል ያለው ውዝግብና ንትርክ እጅግ የሚያሳዝን ምዕመናንንም ቅር የሚያሰኝ ሆኖ እንመለከተዋለን ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ሰላም እየጸለየች ራሷ ግን ሰላም እንዳይኖራት የሚያደርጉ ሁሉ ተግባራቸው ትክክል አለመሆኑን ተረድተው ሰላምን ሊፈልጉ ያስፈልጋል" ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፡ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም" ይላልና የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ። ኤር. ፳፱፥፲፩-፲፪ ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችና ምዕመናን እግዚአብሔር ሰላምን እንዲሰጥ መጸለይ ፤ ማስተማር አለባቸው። ይህ ከሆነ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነውና ሰላምን ያድለናል ። ሰላምን ፈልጉ ስለ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ተብሎ ተጽፎአልና ኤር. ፳፱፥፰ ።

ከዚህ ጋር እርስዎ ሊቀ ዲያቆን መሆንዎን ከስምዎ ጋር ገልጸዋል እንዲህ ከሆነ የሚመሩዋቸው ዲያቆናት ሰላማውያን እንዲሆኑ ስለ ሰላምም እንዲጸልዩ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ዲያቆናት የሰጠውን ትዕዛዝ ማስጠናትና እንዲፈጽሙ ማድረግ አለብዎ ቃሉም የሚከተለው ነው ። "ዲያቆናት ጭምቶች በሁለት ቃል የማይናገሩ ፤ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጐመጁ ነውረኛ ረብ የማይወዱ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል ።

እነዚህም ደግሞ አስቀድመው ይፈተኑ ከዚያም በኋላ ያለነቀፋ ቢሆኑ በዲቁና ሥራ ያገለገሉ ፩ኛ ጢሞ. ፫፥፰-፲" ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ትዕዛዝ ጠንቅቀው የጠበቁ ከሆኑ ጭቅጭቅ ምቀኝነትና ንትርክ ሊያጠቃቸው ስለማይችል በትዕግሥት ሊያገለግሉ ይችላሉና እርስዎ ያለብዎን መንፈሳዊ አደራና ኃላፊነት ለመወጣት መትጋት አለብዎት እንጂ ሌላውን ብቻ ማማረር የለብዎትም ።

ሌላው ምክንያትም ክህነት ያለጥሪ ለሥጋዊ መተዳደሪያ ያህል ብቻ ስለሚሆኒ የተቀደሰ አገልግሎት ለማበርከት አይቻልምና የእግዚአብሔር ጥሪ ለካህናት እንዲሆን መጸለይ አስፈላጊ ስለሆነ ሁሉም ሊጸልይ ይገባል ።

፪ኛው ጥያቄ ደግሞ ለክህነት የምትሆን ሚስት አጣሁ ብለው ያቀረቡት ነው ። መቼም በአዲስ አበባ ለእርስዎ የምትሆን ሚስት ጠፋች ማለት አንችልም ። በእርግጥ እርስዎ እንደገለጹት በየሳምንቱ የሚቀየሩበት የተለያየ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል ።

፩ኛ እርስዎ የሚሠሩት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ስለሆነ የደመወዝ ዝቅተኝነት ይኖራል ብላ ስለምትገምትና በጥቂት ደመወዝም እንደ ጓደኞቼ መሽቀርቀር አልችልም የሚል ፍርሀት ስለሚያድርባት ።

፪ኛ የእርስዎ ምርጫ ቀድሞውኑ ትክክል አይመስለኝም ። ምክንያቱም ለሚስትነት የመረጡዋትን ሴት ምን ዓይነት መለኪያ አግኝተው መረጡዋት ። በጠባዩዋ? በመልኳ? በሀብትዋ በትምህርቷ? ወይስ በመሽቀርቀሯ እዚህ ላይ ነው መጠንቀቅ አንድ ሁለት ቀን ቤተ ክርስቲያን ስትመጣ ወይም መንፈሳዊ መስላ ስትታየዎ ሚስት ትሆነኛለች መንፈሳዊት ናት ብለው ከሆነ እርሷም ሌላ ለእርስዎ ያልገለጸችልዎ ዓላማ ሊኖራት ስለሚችል በመጀመሪያ የእርስዎን ዓላማ ማወቅና መረዳት ከዚያም በኋላ የአመክሮ ጊዜ ሰጥተው በትዕግሥት ማየት አለብዎት እንጂ እነርሱ ጠባያቸውን እንደሚቀይሩ ሁሉ እርስዎም በየሳምንቱ ምርጫዎን ከመቀየር መዳን አለብዎ ።

እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊት ሚስት ማግኘት አልቻልኩም ስለሚሉት እርስዎ ሌላውን ለማሳመን የሚያስተምሩ ካህን በመሆንዎ በሌላው በኩል ተስማምታችሁ ከጨረሳችሁ የእምነቱን ጉዳይ እርስዎ አስተምረው መክረው አሳምነው ወደ እውነተኛው እምነት ሊመልሷት ይችላሉ እንጂ በተረፈ በሁሉም የተሟላ ጠባይ ያላት ሚስት ማግኘት ስለማይቻል አንዳንዱን ጥቃቅን ሁኔታ እየተግባባችሁ ማስወገድ ትችላላችሁ ።

ከዚህም ጋር ለሚስትነት ምርጫ ሲጀምሩ ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ ቢኖር እንደአቅምዎ እንደኑሮዎ እንጂ እንዲያው ደስ ያለችዎትን ሁሉ ላግባሽ ማለቱ አግባብ አይደለም ። መልካም ሚስት የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነች ከምርጫዎ ጋር የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲጨመር መጸለይም አለብዎ ምሳሌ ፲፱፥፲፬ ።

በሌላ በኩልም በመጨረሻው በሶስተኛው ጥያቄዎ ላይ እንደገለጹት የጣት ቀለበት ፡ የጆሮ ጉትቻ ፤ የአንገት ሀብል ቦርሳ የመሳሰሉትን ሁሉ ለመግዛትና ለማሟላት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ነገር እንዲቀር እንድንተባበርዎ የገለጹ በመሆኑ በዚሁ ምክንያትም ጭምር ሊሆን ይችላል ።

በዚህ አጋጣሚ ወደ ሶስተኛው ጥያቄ መልስ እንግባና የሴት ልጅ ማጌጥ ፡ መልበስ ከወንዶች ይልቅ ያስፈልጋታል ፡ ምክንያቱም እስከአሁን ድረስ ባለው የአገራችን ባህል ሴት ልጅ ለሚስትነት ትለመናለች እንጂ ባል እንዲሆናት አትለምንምና ስለዚህም ለመታጨት ማጌጥ ያስፈልጋታል ፤ ለሴት ልጅ ማጌጫ የተጀመረውም በቅዱሳት መጻሕፍት ትዕዛዝ ጭምር እንደሆነ እንመለከታለን ።

፩ኛ/ ይስሐቅ ርብቃን ሲያገባት የብርና የወርቅ ጌጥ ልብስም እንደሰጣት ዘፍጥ. ፳፬፥፶፫ ።

፪ኛ/ ማንም ሰው በሠራተኛነት የቀጠራትን ሠራተኛ እንኳ ቢድር የሚዳሩ ሴቶች ልጆች ሊደረግላቸው የሚገባውን ሊያደርግላት እንደ ታዘዘ ዘፀአት ፳፩፥፱ ።

፫ኛ/ ማንም ሰው ያልታጨችውን ድንግል ቢያስታት ወላጆቹዋና እርስዋ ፈቃደኛ ከሆኑ ማጫዋን ሰጥቶ እንዲያገባት ወላጆቹዋና እርስዋ ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን ደናግልን ሲያጩ ለመጣያ እንዲሰጥ የታዘዘውን ክፍያ ከፍሎ እንዲያሰናብታት ። ዘፀአት ፳፪፥፲፮-፲፯ ተዘርዝሮ ተገልጾአል ። ስለዚህ እርስዎም የሚያጩዋትን ድንግል የሚገባትን ጌጥ መስጠት አለብዎት ምንአልባት የሚያጩዋቸው በየሳምንቱ የሚሸሹዎትም በዚህ ምክንያት ጭምር እንደሆነ በጥንቃቄ ያስቡበት ሚስት ለማግባት ማስጌጥ ተገቢና የራስም ክብር ነውና ።

ለመሆኑ ሳያገቡዋት ያለጌጥ ፡ ያለ ልብስ ያግቡዋት ካገቡዋት በኋላስ አያስጌጡዋትም ማለት ነው ። ገና ሳያገቡዋት ለማልበስና ለማስጌጥ የተቸገሩ ካገቡዋት በኋላስ ቆዳ አልብሼ ልግዛሽ ሳይሉዋት ይቀሩ አይመስለኝምና ባይሆን የምንተባበርዎ ከመጠን ያለፈ የተንዛዛ ድግስን ከአቅም በላይ የሆነ የጥሎሽ ስጦታ መጠየቅን ለማስቀረት እንጂ ከአንገት ሀብል እስከ ጆሮ ጉትቻና የሕጋዊ ጋብቻ ምልክት የሆነውን ቀለበት ለማስቀረት አንተባበርዎትም ። የቤተ

ወደ ገጽ ፳፩ ዙሯል



www.ethiopianorthodox.org

# “ጨውና የሕይወት ጣዕሙ”

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ጨው ከውቅያኖሶች ከባሕሮች ከሐይቆችና ከከርሠ ምድር የሚገኝ መሆኑ ቢታወቅም ቅሉ በቀድሞ ዘመን ቴክኖሎጂው (ጥበበ እድ) እንደዛሬው የረቀቀ ባለመሆኑ አንድ መሐለቅ ወርቅ በአንድ መሐለቅ ጨው ይለወጥ እንደነበር ከታሪክ መዛግብት እንረዳለን ።

በልዩ ልዩ አህጉር ዘንድ ጨው በሰው ዘር አስተሳሰብ ላይ ምን ያህል ጉልህ ማህተም እንዳተመና ለእያንዳንዳችን ሕይወትም ምን ዓይነት ጥቅም እንደሚሰጥ ከዚህ በታች እንመለከታለን ።

ካሲዮዶረስ የተባለው የሮም አስተዳዳሪ አንድ ጊዜ ስለወርቅና ስለጨው እንዲህ ሲል ተናገረ ፤

“ወርቅን የማይፈልጉ ጥቂቶች ሊኖሩ ይችላሉ ጨውን ግን የማይፈልግ አንድም አይገኝም”። በዚያን ዘመን ውድና ብርቅ ተፈላጊም የነበረው ጨው ከእስቲያ እስከ ሮም ድረስ በአንድ በተወሰነ ጎዳና ብቻ በወታደሮች ታጅቦ ይጓጓዝ ስለነበረ የዚያ መንገድ ስም “የጨው ጎዳና” ተብሎ ተሰየመ ለአጃቢዎቹ ወታደሮችም አገልግሎት የሚከፈለው ገንዘብ (ሳለሪየም) (ደመወዝ) ማለት የጨው መግገር ተብሎ ሊሰየም ቻለ ። በሂማሊያ ተራራ ውስጥ ካሉት አገሮች መካከል በአንዷቷ ፣ ከጨው በተሠሩ ቅንስናሽ (ሣንቲም) ገንዘቦች ሕዝቡ ይገበያይበት እንደነበር ማርኮፖሎ የተባለው ተጓዥ ገልጾታል በአገራችንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሞሌ ጨው መገበያያ እንደነበር ከታሪክ ማኅደር ብቻ ሳይሆን የዕድሜም ባለጸጎች ከሆኑ አባቶች መረዳት እንችላለን ።

ከታሪክ ማኅደር ደግሞ የሰው ዘር ጨውን ከዋጋው በላይ ግምትና ክብር በመስጠት ማስተዋልን ጥበብን ፣ ወላድነትን ፣ እንግዳ ተቀባይነትንና ቅድስናን የሚያጎናጽፍ ነው ብሎ ሲመለከተው እናገኘዋለን ። ሆሜር የተባለው ባለቅኔ ጨውን “የመለኮት ስጦታ” ብሎ ሲሰይመው ፕሌቶ የተባለው ፈላስፋ ደግሞ በአማልክት የተወደደ ክቡር ዕቃ ብሎ ሲጠራው እናገኘዋለን ።

1/ ዘላኖች፡- ጨው የሰጣቸውን ሰው አይቃወሙትም አይጣሉትም ነበር ።

2/ እስላሞች፡- ለሙሽሮቻቸው ጨው የተነሰነሰበት ዳቦ በመስጠት ዕድሜልካቸውን ደስተኞችና ጤናማዎች እንዲሆኑላቸው የመልካም ምኞታቸው መግለጫ ምልክት መሆኑን እንገነዘባለን ።

3/ ኢትዮጵያውያን፡- ጨው በተለይም የአሻል ጨው መድኃኒትነት አለው ብለን እናምናለን ።

4/ አይሁዶች፡- ቃልኪዳናቸውን የሚያጸኑት ጨው በመለዋወጥ ነበር ።

5/ በቀደሙት ዘመናት፡- ድል አድራጊው ጦር ሠራዊት ከጠላት ከተማ በገባ ጊዜ ያች ከተማ ዳግም እንዳታንሰራራ ጨው ይነሰንስባት ነበር ።

6/ ግሪኮችና ሮማውያን እንዲሁም አይሁዶች ፡- ጨው የተነሰነሰበት መሥዋዕት ቅዱስ ነው ብለው ያምኑ ነበር ።

በዚህም መሠረት የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የንጽሕናና የቅድስና ምልክት ነው ተብሎ የሚገመተውን ጨው በክርስትና ጊዜ ከተጠማቂው አፍ ውስጥ ታስይዘው ነበር ይባላል ።

በአንጻሩ ደግሞ ጨው ማፍሰስ የመጥፎ ዕድል ምልክት ምክንያት ነው ተብሎ ስለሚገመት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር በጸሎተ ሐሙስ ምሽት የበላውን የመጨረሻዋን ራት ሊዮናርዶ ዳቪንቺ የተባለው ዝነኛና ስመጥሩ ሠዓሊ በቀረጸው ሥዕል ከአስቆሮቱ ይሁዳ ፊት በገበታው ላይ የጨው ብልቃጥ ተዘቅዝቆ ሊታይ በቅቷል ።

ጨው በፋብሪካ ውስጥ ለሰው ልጆች የሚያበረክተውን ጥቅም እንመልከት ። ጨው ከምግብ አጣፋጭነቱም በላይ በጨውነቱ ወይም በሁለቱ ንጥረ ነገሮች ሶዲየምና ክሎሪን ለየብቻቸው በፋብሩካ ውስጥ ገብተው የሚሰጡት ጥቅም እጅግ ብዙ ነው ። የሰው ልጅ በብዛት ከሚጠቀምባቸው አምስት ጥሬ ዕቃዎች ጨው ፣ ኖራ ፣ ድኝ ፣ ከሰልና ፣ ነዳጅ (ፔትሮሊየርም) ብልጫውን ይዞ የሚገኘው ጨው ነው ። ለጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፣ ለመንኰራኩር ነዳጅ ለቁንጅና ቅባቶች ለቀለማቀለም ለፎቶግራፎች ለሳሙና ለሸክላ ሥራ ለባትሪ ለሙጫና ማዳበሪያና ተባይ ማጥፊያ ሲቀመሙ ጨው ይገባባቸዋል ። ለፈንጅ ለበረዶ ማቅለጫና ለማቀዝቀዣ በተለይም ከመሬት ውስጥ እንደ ድንጊያ ተፈልፍሎ የሚወጣው ይጠቅማል ።

አደገኛውን የሬዲዮ አክቲቭ ዝቃጭ በከርሠ ምድር ውስጥ በሚገኝ የጨው ጉድጓድ ውስጥ መቅበሩ አካባቢያችን በዝቃጩ ከመበከል ያድናል ተብሎ ይገመታል ። በተጨማሪም የጨው ጉድጓዶች ከተባይ ነጻ በመሆናቸውና በአየር ጠባያቸው እህልን መጻሕፍትንና ጥንታዊ ቅርሳቅርሶችን በደንብ ለመጠበቅ ዓይነተኛ ሥፍራዎች መሆናቸው ስለተደረሰበት ለእህል ጎተራነት ለቤተ መጻሕፍት ወመዘክርነት እንዲያገለግሉ ጥናቱ እየተካሄደ ነው ። ጨው ከላይ የተመለከቱትን ዓይነት አገልግሎቶችና በፋብሪካ ውስጥም የሚሰጠውን ጥቅም ብንቆጥር አሥራ አራት ሺህ ስለሚደርስ ሌሎች ማዕድናት ከሚሰጡት ሁሉ እጅግ ብልጫ እንዳለው እንመለከታለን ።

በአስተሳሰባችንና በፋብሪካ ውስጥ የሚሰጠውን ጥቅም ተመልክተነዋል ። በአካላችን ላይስ ምን ዓይነት ጥቅም ወይም ጉዳት ያደርስ ይሆን ? እንደሚታወቀው ሁሉ ጨው የሶዲየምና የክሎሪን ቅንብር ነው ። ሶዲየም ማዕድን ሲሆን በባሕርዩ ከውኃ ጋር ሲገናኝ ከመቅጽበት ይነድዳል ። ክሎሪን ደግሞ በጣም አደገኛና ለሞት የሚያደርስ ጋዝ



ነው ። የሚያስገርመው ግን የሁለቱ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ውጤት የሆነውን ጨውን ስንመገብ ሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ የተባለ አደገኛ ነገር ከሆዳችን ይፈጠራል ። ይሁንና አፈጣጠራችን ግሩምና ድንቅ ስለሆነ መዝ ፻፴፱ ፣ ፲፬ ይህ መርዝ አይጎዳንም እንዲያውም ጨውም ለሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነው ። ሁኔታውን ረጋ ባለመንፈስ እንመልከተው ከእያንዳንዳችን ሰውነት (አካል) ውስጥ ፰ መሐለቅ ጨው ይገኛል ። ሶዲየም የተባለው አንዱ የጨው ንጥረ ነገር ለጡንቻ መሳሳብ ለልብ ትርታ ለነርቮች እንቅስቃሴ ሰውነት ገንቢ የሆኑትን ፕሮቲን ለመፍጨት ይጠቀማል ። የደም ሴሎች ጨው ከሌለበት ፈሳሽ ውስጥ ቢዘፈዘፉ እንደ ፊኛ ጢ እያሉ ይፈነዳሉ ። ጨው በእያንዳንዱ ሴሎቻችን መካከል የሚዘዋወረው ውኃ ምግብ እንዲያደርስ ቆሻሻም እንዲያስወግድ ይረዳል ። ጨው በሽታ የመከላከል ኃይላችንን ያጠነክረዋል ። ያለጨው ግን የማስታወክ የመንቀጥቀጥ ሽባ የመሆንና ሞትንም ያስከትላል ።

ሆኖም አፈጣጠራችን ነቢዩ ዳዊት እንዳለው ግሩምና ድንቅ በመሆኑ ብዙ ጨው ያለበት ምግብ ስንመገብ ኩላሊታችን በቆሻሻ መልክ እንዲወገድ ፣ ጥቂት ጨው ያለበት ምግብ ስንመገብ ግን በምትኩ ውሃን ከሰውነታችን በማስወገድ የሰውነታችን ሁኔታ እንዳይዛባ ሚዛን ጠብቆ እንዲኖር ያገለግላሉ ።

ከላይ ስለጨው የተነገረውን ስናጠቃልል የማይፈለገውን የሚያስወግድ የምግብ አጣፋጭነቱን ለመሥዋዕትነትም ቅድስናን የሚሰጥ ፣ መድኃኒትነቱንና የቃልኪዳን ማረጋገጫነቱን እንመለከታለን ። የሰው ዘር በኃጢአት ምክንያት ከአምላኩ ጋር ተራርቆና ተጣልቶ በነበረበት ሰዓት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ቅዱስ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና በማስታረቅ በደሙ ለመሠረታት አዲስ ኪዳን ዕውነተኞች ምስክሮችና የምሥራች አብሳሪዎች የነበሩትን ደቀመዛሙርቱን ነው ። “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ” ብሎ የሰየማቸው ማቴ. ፭.፲፫። በዚህም መሠረት በዚያን ጊዜ የነበሩት ሐዋርያት ከዚያም በኋላ በየዘመኑ የተነሱትና የሚነሱት የወንጌል መምህራን በአጠቃላይም ክርስቲያኖች በሙሉ የምድር ጨው ናችሁ ተብለው የሚጠሩበት ምክንያት ይህን የተጎሳቆለውንና አልጫ የሆነውን ዓለም እነእርሱ እንደ ጨው እየሟሙ የሚያጣፍጡት ፣ ከሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚጠሩት ዕውነተኛውን መድኃኒቱን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደውን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕትም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመለከቱና በእርሱም እንዲመላለሱ የሚያስተምሩ በመሆናቸው ነው ።

ከናሽናል ጂኦግራፊክ መጋዚን
ቅጽ ፻፶፪ ቁጥር ፫
እንግዳ ወርቅ ጥሩነህ

# ሰላም ለሁላችሁ...

ከገጽ ፩ የዞረ

ርላማ አባሎች ተካፋይ የሆኑበት የዓለም ሰላም ምክር ቤት በሃቫና ባካሄደው ስብሰባ አዲስ የዓለም ጦርነትን ለማስወገድና ዴታንትን ለመንከባከብ የበኩሉን ጥረት አድርጐ ነበር የኑክሊየር ሚሳይሎችና ባይናሪ ፈንጂዎች እንዳይሠሩ ተቃውሟቸውን በመግለጽ በኢጣሊያ ፣ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሣይ ፣ በምዕራብ ጀርመን በሆላንድና በሌሎችም የአውሮፓ አገሮች ሰላማዊ ሰልፎች ተደርገዋል ። እንዲሁም በኖርዌይ ሴቶች ጥሪ መሠረት የ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ በሚል መመሪያ የሚታወቅ ከፍተኛ የተቃውሞ ጉዞ ተደርጓል ። ሰልፈኞቹ በአውሮፓ ውስጥ የኑክሊየር መሣሪያዎችን መተከል የሚያወግዙ መፈክሮችን አንግበው ዴንማርክን ምዕራብ ጀርመን ሆላንድን ፣ ቤልጅግንና ፈረንሣይን በማቋረጥ ከከፐንሃገን እስከፓሪስ ድረስ ያደረጉት ፵፭ ቀናት የፈጀው የ፩ሺ፩፻ ኪሎ ሜትር የእግር ጉዞ ዓለም ስለሰላም ምን ያህል እንደሚጨነቅ ያስረዳል ። ዓለም ስለሰላም ይህን ያህል ሌት ተቀን የሚጨነቀው ወዶ አይደለም ። በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች የተፈጸሙት እልቂቶች ትዝ እያሉት ነው ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ብቻ የወደመው ንብረትና የአለቀው ሕዝብ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ሲዘገንን የሚኖረው ነው የአሜሪካን ኮሚንስት ፓርቲ ጸሐፊ ገስሆል “ኢምፔሪያሊዝም ዛሬ” በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለጹት ከ፶ ሚሊዮን በላይ ሕይወት ሲጠፋ ፴፭ ሚሊዮን ቆስሏል። የወደመውን ንብረት ለመግለጽ ግን አኃዞችን መደርደሩ ያሰለቻል ። አሜሪካ በዚህ ጦርነት ወቅት በሂሮሽማና በናጋስኪ ላይ የጣለቻቸው ሁለት ቦንቦች ብቻ ፪፻፲ ሺህ ሰዎችን ወዲያውኑ ሲገድሉ ከ፮፻፴ ሺህ ሕዝብ በላይ የሚበልጠውን በመርዝ ጤንነቱን በክሏል ያ ጠንቅ ዛሬ በዚያ አካባቢ ብዙዎችን ነዋሪዎችና ተወላጆች ሽባ ፣ ዓይነ ስውርዲዳና ደንቆሮ አድርጓቸዋል ።

በጠቅላላው እ.ኤ.አ. ከ፲፰፻፸ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፩፻፳፩ ጦርነቶች በአፍሪካውያን ላይ ተካሂደዋል ። በዚህም ሳቢያ ፫፻ ሺህ ሰዎች በግፍ እንደተጨፈጨፉ ገስሆል ይናገራል ። በዘመናችን በተነሡት ልዩ ልዩ ጦርነቶች ፰ ሚሊዮን ሕዝቦች ተደምስሰዋል ፩፻፲ ሚሊዮን ሽባ ሆነዋል ። ፲፩ ሚሊዮን በጋዝ ጭስ ታፍነው አልቀዋል ። ፫ ሚሊዮን ከአውሮፕላን በሚጣሉ ቦንቦችና ናፓል ቦንቦች ከምድረ ገጽ ጠፍተዋል ። ፫፻፶ ሺህ የደቡብ ቬየትናም ሕፃናት በናፓል ቦንብ ጋይተዋል ። ዓለም ዛሬ ሰላም ሰላም እያለ የሚጮኸው ከዚህ በአጭሩ የተገለጸው ዓይነት እልቂት እንዳይገጥምና ፍጡራንን ከጦርነት ስጋት ለማዳን ነው ።

ተከታዩን በገጽ ፳፬ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ

# የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት ፯

በዚህ ትምህርት መድረሻ ፊደላቸው ሀ- ሣልስ ለ- ራብዕ ሐ- ሐሙስ መ/ ሳብዕ የሆኑ ስሞች (ቃላት) እንዴት እንደሚረቡ እንመለከታለን ።

| ሣልስ | | ራብዕ | | ሐምስ | | ሳብዕ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጸላኢ | ጠላት | ምህርካ | ምርኮ | ጽጌ | አበባ | መሰንቆ | ማሲንቆ |
| መድኃኒ | አዳኝ | እንዚራ | በገና | ጽዋዔ | ጥሪ | ገቦ | ጐን |
| መርዓዊ | ሙሽራ | ጥዒና | ጤንነት | ግልባቤ | ሽፋን | ማዕዶ | መዝጊያ |
| ኖላዊ | እረኛ(ጠባቂ | ታዕካ | ሰገነት (አዳራሽ) | ይባቤ | እልልታ | መርሖ | መክፈቻ (ቁልፍ) |
| ዓዲ | ገና | ዐመፃ | በደል (ግፍ) | ሱታፌ | አንድነት | ውዕቦ | አምባር |
| መፍቀሪ | ወዳጅ | ሐራ | ጭፍራ (ወታደር) | ህላዌ | ኑሮ | ፀልቦ | መስቀል |
| | | | | ጽማዌ | ድንቁርና | አበሞ | ሽቱ |

መክሥት ፡- ከዚህ በላይ ያጠናናቸው ቃላት ሁሉ መድረሻ ፊደላቸውን ሳይለውጡ የእርባታ መሪዎችን ይቀበላሉ ።

| ምሳሌ (ሣልስ) | | (ራብዕ) | | ሐምስ | | (ሣብዕ) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መድኃኒየ | አዳኜ | ጥዒናየ | ጤንነቴ | ህላዌየ | ኑሮ የ | ገቦየ | ጐኔ |
| መድኃኒከ | አዳኝህ | ጥዒናከ | ጤንነትህ | ህላዌከ | ኑሮህ | ገቦከ | ጐንህ |
| መድኃኒሁ | አዳኙ | ጥዒናሁ | ጤንነቱ | ህላዌኪ | ኑሮሽ | ገቦኪ | ጐንሽ |
| መድኃኒኪ | አዳኝሽ | ጥዒናኪ | ጤንነትሽ | ህላዌሁ | ኑሮው | ገቦሁ | ጐኑ |
| መድኃኒሃ | አዳኟዋ | ጥዒናሃ | ጤንነቷ | ህላዌሃ | ኑሮዋ | ገቦሃ | ጐንዋ |
| መድኃኒነ | አዳኛችን | ጥዒናነ | ጤንነታችን | ህላዌነ | ኑሮአችን | ገቦነ | ጐናችን |
| መድኃኒክሙ (ተባ) | አዳኛችሁ | ጥዒናክሙ (ተባ) | ጤንነታችሁ | ህላዌክሙ (ተባ) | ኑሮአችሁ | ገቦክሙ | ጐናችሁ |
| መድኃኒክን (አን) | » | ጥዒናክን (አን) | » | ህላዌክን (አን) | ኑሮአችሁ | ገቦክን (አን) | ጐናችሁ |
| መድኃኒሆሙ (ተባ) | አዳኞቻቸው | ጥዒናሆሙ | ጤንነታቸው | ህላዌሆሙ (ተባ) | ኑሮአቸው | ገቦሆሙ(ተባ) | ጐናቸው |
| መድኃኒሆን (አን) | አዳኞቻቸው | ጥዒናሆን (አን) | » | ህላዌሆን (አን) | » | ገቦሆን (አን) | » |

አሁን ዐረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል እነዚህን ቃላት እናጥና ።

እፎ እንዴት ምት ባል ሠናይ መልካም (ጥሩ)

### ዐረፍተ ነገር

| | |
|---|---|
| መኑ ውእቱ መድኃኒከ | አዳኝህ ማን ነው ? |
| እግዚአብሔር ውእቱ መድኃኒየ | አዳኜ እግዚአብሔር ነው ። |
| መኑ ውእቱ መድኃኒክሙ (ተባ) | አዳኛችሁ ማን ነው ? |
| ክርስቶስ ውእቱ መድኃኒነ | አዳኛችን ክርስቶስ ነው ። |
| እፎ ውእቱ ጥዒናኪ | ጤንነትሽ እንዴት ነው ? |
| ሠናይ ውእቱ ጥዒናየ | ጤንነቴ መልካም ነው |
| ሠናይኑ ውእቱ ጥዒናክን (አን) | ጤንነታችሁ መልካም ነው ? |
| እወ ሠናይ ውእቱ ጥዒናነ | አዎ ጤንነታችን ደህና ነው |
| እፎ ውእቱ ህላዌሁ | ኑሮው እንዴት ነው ? |
| ሠናይ ውእቱ ህላዌሁ | ኑሮው ጥሩ ነው |
| ምስለ መኑ ውእቱ ህላዌሃ | ኑሮዋ ከማን ጋር ነው |
| ምስለ ምት ውእቱ ህላዌሃ | ኑሮዋ ከባል ጋር ነው ። |

### ግብረ ቤት — የቤት ሥራ

መድረሻቸው ሣልስ ራብዕ ፣ ሐምስ ፣ ሳብዕ ከሆኑ ቃላት ከዚህ በላይ ባጠናች ሁት መሠረት ለማርባት ሞክሩ ።



# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



አዘጋጅ

ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

እንዳሁኑ ዘመናውያን ት/ቤቶች ሳይ መሠረቱና ሳይስፋፉ የሀገራችን ወጣ ቶች የዕውቀት ብልጭታ የሚያዩት ፣ ማንበብና መጻፍ ፣ ሥዕልና ቅርጻቅርጽ መሥራት የመሳሰሉትን የተግባረ እድ ሙያዎች የሚያጠኑትና የሚለማመዱ ት በጥንታውያን መንፈሰውያን ት/ ቤቶች ነበር ። ቅኔ የመቀኘትን የዜማ ፣ የማጥምና የመዝሙር ሙያዎችን የመሳ ሰሉትን ሁሉ የሚያጠኑት በነዚሁ ጥን ታውያን ት/ቤቶች በትምህርት ላይ በሚ ቆዩበት ጊዜ ውስጥ እንደነበርም የሚታ ወስ ነው ።

ወጣቶች በተወለዱበት አካባቢ የፊደ ላትን ቅርጽ ከለዩና የንባብ ትምህርታ ቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በትምህርት እየ ጐለመሱና አእምሮአቸው እየጠና ሲሄ ዱ ከፍተኛ ትምህርት ካላቸው መምህ ራን የተሻለ ዕውቀት ለመገብየት ሲሉ ከተወለዱበት አካባቢ ራቅ ብለው ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ከፍተኛ ትምህርታቸ ውን ይከታተላሉ ። ይህም በአንድ ቦታ ብቻ ተወስነው ሳይሆን እንደሚማሩት የትምህርት ዓይነትና እንደፍላጐታ ቸው መጠን ከቦታ ፡ ወደቦታ ከአንዱ ክፍለ ሀገር ወደሌላው እየተዘዋወሩ ነው ። ለምሳሌ ከዜማ ወደ ቅኔ ከዚያም ወደአቋቋምና መጻሕፍት ትርጓሜ ቤት ወዘተ እያሉ ብዙ ሀገሮችን ያዳርሳሉ ።

ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን ከወላጆቻ ቸው ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ ምግባቸ ውንና ልብሳቸውን የሚያገኙት ከቤተ ክርስቲያንና ከምእመናን ነው ። ከዚያ በተረፈ ግን ብራና ፍቀው ፣ ቀለም በጥብ ጠው ፡ ብርዕ ቀርፀው መጽሐፍ እየጻ ፉና እየደጎሱ ፣ ሰሌን እየሠሩ ያንን በመ ሸጥ በሚያገኙት ገቢ የሚጠቀሙ ነበሩ ምእመናኑ ተማሪዎችን ከመውደዳቸው የተነሣ የዕለት ምግባቸውን ከመስጠት አልፈው ቢታመሙ የሚያስታምሙ ቢቸገሩም እንደልጆቻቸው አድርገው የሚረዱ አሉ ። ተማሪዎቹም ከምእ መናኑ ያገኙትን ምግብ ጥሬውን ራሳ ቸው አብስለውና አዘጋጅተው የበሰለ ውንም እንደሁኔታው አዘጋጅተውና አቀነባብረው እንደ ጓድ እንደጓዳቸው በኅብረት ይመገባሉ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ርስበርሳቸው የሚኖራቸው መግባባትና መከባበር ተመልካችን የሚስብና እጅግ የሚያስደስት ነው ። አንዱ ሌላውን የሚጠራው አይዋ ፣ ጓዴ ክንዴ ወዘተ በሚል የአክብሮት ስም ነው ። ይህ እርስ በርሳቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገ ልጥ ሲሆን ለመምህራቸው የሚያደርጉ ለት አክብሮት ደግሞ በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ "አንድ ቀለም የነገረህን እንደ አባትህ ፡ ሁለት ቀለም የነገረህን እንደፈጣሪህ አክብረ ው" በሚለው የአባቶች ዘይቤ ላይ የተ መሠረተ ነው ይህም ለዘመኑ ወጣቶቻ ችን መልካም አርአያና ምሳሌ ሊሆን ይችላል ።

በጥናት ረገድ ከአንዳንድ እግረ ተማ ሪዎች በቀር አብዛኛዎቹ የመማገጥ ጠባ ይ አይታይባቸውም ይልቁንም ትምህ ርታቸውን ስለሚወዱ ወንበራቸውን አክብረው (የትምህርት ተራቸውን ተ ጠባብቀው) በፕሮግራሙ መሠረት እየተ ተገኙ ይማራሉ በሚገባም ያጠናሉ ። ቆሎ ሲቆሉ ኮቸሮ ሲያኮችሩ) (ፍርፍ ር ሲያፈረፍሩ) ተኝተውም ሆነ ተቀም ጠው አፋቸው ከቅፀላ አይቦዝንም የተ ማሪዎቹ መኖሪያ አንድ ላይ ስለሆነ ደካማው ብርቱውን ሰነፉ ጐበዙን እያ የ ይበረታል ያወቀ ላላወቀ ያሳው ቃሉ ፡ የገባቸው ላልገባቸው ያስረዳሉ ። በዚያውም ላይ መምህራኑና ተማሪዎቹ የሚኖሩት በዚያው በት ቤቱ ውስጥ በ መሆኑ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ስለሚደ ረግ ለውስልትና ቦታ አይኖረውም ።

ጥንታዊ መንፈሳዊ ተማሪ የሚማ ረው ይህን አውቄ ይህንን አገኛለሁ በ ዚህን ያህል ደመወዝ እቀጠራለሁ በማ ለት ሳይሆን በገበየው ዕውቀት አገሩንና ቤተ ክርስቲያኑን በነፃ ለማገልገል በገ ባው ቃል ኪዳንና ባለው ቀና አስተሳሰ ብ ጭምር ስለሆነ ቃለ እግዚአብሔር እየጣመው የዕድሚውን ግማሽ የሚያሳ ልፈው በትምህርት ቤት ነው ። መምህ ራኑም ተማሪዎቻቸውን እንደወለዷ ቸው ልጆች ከዚያም በላይ ስለሚወዷ ቸው ያለደመወዝ በነፃ ሌትና ቀን ሲያስ ተምሩ አይሰለቹም ።

ዛሬስ ይህ ሁኔታ እየቀጠለ ነው? ወይስ መልኩን ለውጦ ይሆን ? እንደጥንቱ



www.ethiopianorthodox.org

ቆሎ እየቆረጠሙ ከጥሬው ጋር ቃለ እግዚአብሔር የሚያጣጥሙ እውነተኛ ደቀ መዛሙርትስ ይኖሩ ይሆን ?

ማቁንና አጎዛውን ለብሶ አኩፋዳውን አንግቦ "በእንተ ስማ ለማርያም" እያለ ወደሠፈራቸው የሚመጣውን የቆሎ ተማሪ የሚያስተናግዱና ምሳና እራት ሰጥተው የሚሸኙ እናቶችና አባቶችስ አሉወይ ? በደመወዝ ሳይሆን በነፃ ስለ ጽድቅ ብለው የሚያስተምሩ መምህራንስ ምን ያህል ናቸው ? ወጣቶችስ እንደጥንቱ ችግሩን ተቋቁመው መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ለመከታተል ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው ? ካልሆነስ ተምረው በአባቶች እግር የሚተኩ ወጣቶችን እንዴት ማግኘት ይቻላል ? የሚለው ጥያቄ ወቅታዊ ስለሆነ መልስ የሚያስፈልገው ነው ።

ኝቼ እኖራለሁ እያለ ገሸሽ የሚለው እየበረከተ በመሄዱ ነው ።

2. የኑሮ ሁኔታ እያደገ ሲሄድ ጥንት የቆሎ ተማሪዎችን በነፃ እየቀለቡ የሚረዱ,ቸው ሁሉ ምናልባት በዚሁ ይዞታቸው መቀጠል ባይችሉ ይሆናል ።

3. ጥንታዊ ትምህርት ለተማሩት ሊቃውንት የሚገባ እንክብካቤ አለመደረጉና በቂ መተዳደሪያ አለማግኘታቸው በእነሱ እግር ለመተካት በትምህርት ላይ ያሉትን ወጣቶች ተስፋ ሊያስቆርጣቸው ስለሚችል እንዲያቋርጡና ዓላማቸውን እንዲለውጡ ሳያደርጋቸው አልቀረም ።

4. መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት የጐደላቸው አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች "የቄስ ትምህርት" የሚል ቅጽል በመስጠትና መልካሙን ስም እንደመጥፎ በማስመ ራን አብዛኛዎቹ በግል ፈቃዳቸው በነፃ የሚያስተምሩ ሲሆኑ ከተማሪዎቹም አብዛኛዎቹ እንደዚሁ ከየቤተሰቦቻቸው እየነበሉ የሚመጡ ከመሆናቸው በቀር ዕቅድ ወጥቶላቸው ምርጫቸውን አስተካክለው የሚመጡ ባለመሆናቸው የተሻለ አጋጣሚ ሲያጋጥማቸው ሊያቋርጡ ስለሚችሉ ነው ።

6. በገጠር ያሉት መምህራን ደመወዝ የሌላቸው ከመሆናቸው የተነሣ ወደከተማ እየመጡ በአንዳንድ አልባሌ ሥራ ተሰማርተው እዚሁ በመቅረታቸው ወንበራቸው እየታጠፈ ጉባዔያቸው እየተፈታ ተማሪዎች እየተበተኑ ነው ።

7. በበጀት የተቀጠሩ መምህራን ጡረታ ሲወጡ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አብዛኛውን ጊዜ በጀቱ ለሌላ ሥራ እንዲውል ስለሚደረግ ተተኪ



ጥንታዊው ትምህርት የሚሰጠው በዚህ መልክ ነበር ።

በአጠቃላይ ሁኔታውን ስንገመግም ግን በጥንቱ ይዘት የሚያስተምሩት መምህራንና የተማሪዎቹም ቁጥር እየቀነሰ የሚሄድ ይመስላል ። ለምን ? ቢባል

1. ትምህርቱ ብዙ ዘመን የሚጨርስ ከመሆኑ የተነሣ ከዚህ ይልቅ የዘመኑን ትምህርት ብማር የተሻለ ደመወዝ አግ ሰል በሚያደርጉት የማጥላላት ዘመቻ ምክንያት በተለይ በከተማ ያሉ ወጣቶች መንፈሳዊ ትምህርት ከመማር ወደ ኋላ የሚሉ ይመስላል ።

5. ቤተ ክርስቲያኒቱ ለመንፈሳዊ ትምህርት በቂ ዕቅድና ዝግጅት ካለማድረጓ የተነሳ በገጠር ካሉት መምህ ባለመኖሩ ነው ።

በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው ጥንታዊው መንፈሳዊ ትምህርት ድክመት ያሳየ የሚመስለው ። በአንዳንድ ቦታም የዜማና የቅኔ መምህራን ተማሪ ከማጣታቸው የተነሣ ሥራ ከመፍታት በማለት ከደረጃቸው ዝቅ ብለው



ፊደል ሲያስቆጥሩና ንባብ ሲያስነብቡ የሚታዩትም ስለዚህ ነው ።

በተለይ በአዲስ አበባ አድባራት በመምህርነት የተመደቡ መምህራን ተማሪ ከማጣታቸው የተነሣ መጽሐፋቸውን አጥፈው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ እንዲወሰኑ ተገደዋል ። ስለዚህም ጥንታዊው ትምህርት እየተዳከመና ተተኪ እየታጣ መሄዱ አያጠራጥርም ታዲያ መፍትሔው ምንድነው ?

1. በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙት ዲያቆናት ወጣቶች እንደመሆናቸው መጠን ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ በትርፍ ጊዜያቸው በየደብሩ በመምህርነት ከተመደቡት መምህራን ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲያጠኑ ቢደረግ ለጥንታዊ ትምህርት መስፋፋት መፍትሄ ከመሆኑም በላይ ቤተ ክርስቲያን የደጀ ጠኚዎች ቦታ ከመሆን አልፋ ዓላማቸውን የሚያውቁት እውነተኞች ካህናት የሚኖሩባት ትሆናለች ።

2. በአሁኑ ጊዜ እንደጥንቱ በየገጠሩ እየተዘዋወሩ ስንቃቸውን በማግኘትና ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የቆሎ ተማሪዎች የመታወቂያ ወረቀት አጥተው በሚዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ ችግር እንዳያጋጥማቸው ጥንታዊ መምህራን ያሏቸው አድባራትና ገዳማት ለተማሪዎቻቸው የመታወቂያ ወረቀት እያዘጋጁ በትክክል ለሚማሩት ተማሪዎች ቢሰጧቸው ያለችግር ስንቃቸውን እያገኙ ለመማር ይችላሉ ። የሚል ግምት አለ ።

3. እንዳለፉት ጊዜያት በልመና ስንቅ እየተማሩ ራስን የመቻሉ ጉዳይ ወደፊት እያከተመ መሄዱ ስለማይቀር ቤተ ክርስቲያን በሁኔታው አስባበት ምእመናኑን በማስተባበርና ለዚህ አገልግሎት የሚውል ርዳታ በመጠየቅ የተወሰነ በጀት አዘጋጅታ በየክፍለ ሀገሩ በየአውራጃውና በየወረዳው የተወሰነ አዳሪ ት/ቤት አቋቁማ መንፈሳዊ ዝንባሌ ያላቸውን ብቻ መርጣ እየረዳች ካላስተማረች ተተኪ መምህራን ማግኘት አይቻልምና ሊታሰብበት ይገባል ። በዚህ ረገድ የአዲስ አበባው ታዕካ ነገሥት በዓታ መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት በምሳሌነት የሚጠቀስ ሲሆን በደብረ ሊባኖስ ያለው የመጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤትም ሌላው ማስረጃ ነው ።

በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚገኘው ይኸው ት/ቤት የብሉያት የሐዲሳትና የሊቃውንት ትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ያሉት ሲሆን ለመምህራኑ ደመወዝ ከመኖሩም በላይ ለተማሪዎቹም ስንቅ የሚሆን የኪስ ገንዘብ እየተሰጣቸው ከሃያ የማያንሱ ተማሪዎች በመማር ላይ ናቸው ። ይህም ቁጥር በገዳሙ ውስጥ ዜማ ፥ ቅኔ አቋቋምና ቅዳሴ የመሳሰሉትን የሚማሩትን ሳይጨምር ነው ት/ቤቱ ለመምህራኑና ለተማሪዎቹ ለያንዳንዳቸው ማደሪያ የሚሆን በቂ ክፍል ያላቸው ሲሆን የጉባዔ መማሪያና የጸሎት ቤት በተሟላ ሁኔታ ተዘጋጅቶለት ይገኛል ። ከዚህም ጋር በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ያለው ተክል ዓይን የሚማርክ ሆኖ ታይቶናል ። ከዚህ አንፃር ግን በጥሩ ሁኔታ የተሠራው ትምህርት ቤት መሠረቱ በመፍረስ ላይ ሲሆን የሚጠግነው ማጣቱ እጅግ አሳዝኖናል "ሰነፍ እረኛ ከቅርብ ትቶ ከሩቅ ይመልሳል" እንደሚባለው ሳይሆን አሁኑን ይታሰብበት በማለት ለሚመለከተው ክፍል ለማሳሰብ እንወዳለን ።

## ቅዱስ ሚካኤል ...

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

ኑን ባለመገንዘብ ድሆችን አይረዳበትም ነበር ። እግዚአብሔር ግን ድሆችን ማበልጸግ ትዕቢተኞች ባለጸጐችን ማደህየት የሚችል አምላክ በመሆኑ የድሀዋን ልጅ ሊያበለጽገው በመውደዱ በተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል አማካይነት የትዕቢተኛውን ባለፀጋ ሀብት ለድሀው ለባህራን አወረሰው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሶ ከመበልጸግ፣ ትዕዛዙን ፈጽሞ መደህየት ይሻላልና። እግዚአብሔርን ያመነ ግን በረከትን አያጣም መዝ. ፴፮፣፲፮ መላእክት በዚህ ዓይነት ሰዎችን ይረዳሉ ፥ ሰዎችን ከታዘዘ መቅሰፍት ከተወረወረ ጦር ይጠብቃሉ ። ይህም በመሆኑ ጠባቂያችንና ጠበቃችን የሆነውን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በታላቅ መንፈሳዊ ሥርዓት እናከብረዋለን ። እኛም የመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ጥበቃ እንዳይለየን ከእኛ የሚጠበቅ ተግባር አለ ።

ጠባቂነቱ እንዲሠምርልን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ ቅዱስ ሚካኤል እንዲረዳን የተቸገሩ ወገኖቻችንን መርዳት በአጠቃላይ መጠበቅ ያለብንን ግዴታ አለመዘንጋት ይኖርብናል። ይኸውም በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልም አታስመርሩት ፥ ዘፀአት ፳፫፥፳ ። ተብሎ እንደተጻፈው ወገናችንን በመርዳት እግዚአብሔርን በቅንነት በማገልገል ፋንታ ኃጢአት እየሠራን ወገናችንን ብንበድል ፥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ፈጻሚ የሆነው ቅዱስ ሚካኤል ስለሚማረር መጠንቀቅ አለብን ።

ቅዱስ ሚካኤልን በችግራችን ጊዜ ብንጠራው ለመርዳት ቸል አይልም ። እነሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ተብሎ ተጽፎአል!

ተስፋ ጥሩነህ

## ቤተ ክርስቲያንና...

ከገጽ ፩፪ የዞረ

ቤተ ክርስቲያንም በበኩሏ ከመንግሥትጉን በመሰለፍ "ድንቁርና ይጥፋ እውቀት ይስፋፋ" በማለት ድርሻዋን ከማበርከት ወደ ኋላ አትልም ። ተምሮ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብር በመሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ኅብረተሰብኡ ከድንቁርና መጋረጃ እንዲላቀቅ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ እንደሆነ አይጠረጥርም ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ

(በከፍያለው መራሂ)

ባለፈው ጽሑፍ በቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ መካከል በፊት የነበረውና አሁንም ያለው የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት ምን ዓይነት ባሕርይ እንደነበረው በአጠቃላይ ለመግለጽ ሞክረናል ።

ዛሬ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በትምህርት በኩል ለኅብረተ ሰብኡ ያበረከተችው አስተዋጽኦ ምን ዓይነት ገጽታ እንደነበረው ከታሪክ ማኅደር ጋር በማገናዘብ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

ለአያሌ ዘመናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ማዳረስን ሀላፊነት ይዛ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኅብረተሰብን ንባብና ጽሕፈት ስታስተምር ቆይታለች ። የትምህርቱም ባሕርይ ሃይማኖትን ፤ የሀገር ፍቅርን ፤ ነፃነትን ፤ እኩልነትንና ፍትሕን ያጠቃልላል ። ይህንም ከኅብረተሰብእችን የብዙ ሺህ ዘመናት የነፃነት ታሪክ ጋር አዛምዶ ለመረዳት ይቻላል ። ደኃ እንዳይበደል ፍርድ እንዳይጓደል የሚፈርዱት ዳኞች በታወቁት የጉባዔ ቤቶች (የትምህርት ተቋሞች) ሕገ መንፈሳዊንና ሕገ ሥጋዊን ጠንቅቀው ያወቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደነበሩ የታወቀ ነው ። በመምህራኑና በደቀመዛሙርቱም መካከል ያለው የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት በወላጆችና በልጆች መካከል ካለው የእውነተኛ ፍቅርና የመከባበር ሁኔታ በምንም ዓይነት ተለይቶ አይታይም ። ይህ ይታወቅ ዘንድ በአባቶች ዘይቤ አንድ ቀለም የነገረ እንደ አባት ፤ ሁለት ቀለም የነገረ እንደ ፈጣሪ መከበር እንዳለበት ለልጆች የግብረ-ገብነትን ትምህርት ያስተምራሉ ።

ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀው በየትኛውም ዓለም የሌለ ፤ በኢትዮጵያ ብቻ ሲሠራበት የኖረ ደቀመዛሙርቱ ትምህርትን ወይም ጥበብን የመቅሰም ፍላጐታቸውን እስከሚያረኩ ድረስ ኅብረተሰብኡ የሚበላውን እየመገበ ፤ የሚለብሰውን እያለበሰ ሳይመረር እንደ አባትና እንደ እናት በመሆን ያስተምራቸዋል ። ይህ ዓይነቱ ባሕልና የትምህርት መርሐ ግብር በየትኛውም ዓለም ያልተለመደና ምሳሌ የማይገኝለት በኢትዮጵያ ብቻ ለረዥም ዘመናት ሲሠራበት የኖረ ፤ አሁንም ያለ ነው ። ይህ ዓይነቱ አሠራር ምንአልባት ወደፊት ታሪክና ምሳሌ ሁኖ ሊቀርብ ይችል ይሆናል ።

ሊቃውንቱም ከዕለት ጉርስ ከዓመት ልብስ በስተቀር ከፍተኛ ዋጋ ሳይጠይቁ እውቀታቸውን በነፃ ለኅብረተሰቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ ኑረዋል ። በእርግጥ ሥርዓተ ትምህርቱ በዘመናችን ካለው የአሠራር እቅድ የተለየ ባሕርይ ነበረው ፤ ከክፍል ወደ ክፍል በማለፍ ወይም ይህን የትምህርት ዓይነት የጨረሰ ይህን ያህል ደመወዝ ያገኛል በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ አልነበረም ፤ ደቀመዛሙርቱ ከጉባዔ ወደ ጉባዔ በመዛወር ለእውቀትና ለጥበብ ብቻ ይጥሩ ነበር ፤ ስለዚህ በትምህርት ዓለም ረዥም ወራት ሰፊ ዘመናት ስለሚደክሙበት ሊቃውንቱ በሊቅነታቸው ሙሉ ሲሆኑ "አራት ዓይና" የሚባል የቅጽል ስም ይሰጣቸዋል ። በዚህ ዓይነት ትምህርት ለምርምር ለሀገር ብልጽግና ፤ ለኅብረተሰብእ ደኅንነት እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ስትመክርና ስታስተምር ኑራለች ፤ ወደፊትም ትሠራበታለች ።

ካልተማሩ እያወቁ ካላወቁ አይጸድቁ እንዲሉ ቤተ ክርስቲያን ለረዥም ዘመናት ኢትዮጵያውያን ወገኖችን ሁሉ ለመብታቸውና ለብሔራዊ ነፃነታቸው እንዲቆሙ ፤ በነፍሳቸው ከዲያብሎስ ተገዥነት ፤ በሥጋቸውም ከወራሪ የቅኝ ገዢዎች ባርነት ፍጹም ነፃ እንዲሆኑ ሕገ መንፈሳዊንና ሕገ ሥጋዊን የሕይወታቸው መመሪያ እንዲያደርጉ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ኅብረተሰብኡን ስትመክር ስታስተምር ኑራለች ።

ትምህርቱንም በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ከፍላ ታስተምራለች ለወጣንያንና ለማዕከላውያን ወይም ለልጆችና ለወላጆች አመች በሆነ መንገድ ፤ ለምሳሌ የምግባረ ሠናይ ትምህርት ለወጣቶች በብሉይ ኪዳን እንደ ተጻፈው በወጣትነትህ ዘመን ፈጣሪህን አስብ የሚለውን መሠረተ ትምህርት ሲሆን ፤ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ልጆች ወላጆቻችሁን ማክበር አለባችሁ ዕድሜያችሁ ይረዝምላችሁ ዘንድ የሚለውን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ። ምግባረ ሠናይ ወይም ግብረ ገብነት እየተባለ የሚጠራው ትምህርት መንፈሳዊ ሕይወት በወጣቶች ላይ አድሮ ይኖር ዘንድ ልዩ ልዩ ምሳሌዎችንና ሕጎችን በመጥቀስ ያስተምሯቸው የነበረ ትምህርት ነው ፤ ከምሳሌዎችም ውስጥ የሲራክን የሰሎሞንን ትምህርቶች በመጥቀስ ያስተምሯቸው ነበር ። በዚያም ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ፍልስፍና ይገልጡላቸው ነበር ፤ ከሕግጋትም ውስጥ የግብረገብነትና የእምነት አንቀጽ ያለበትን ዲዲስቅልያን ያስተምሯቸው ነበር ፤ እነዚሁ ትምህርቶች ግዴታ እንደነበሩና ሁሉም ሊማሯቸው አስፈላጊ እንደነበር የሚያመለክተው አስረጅ "መቅድመ መሀርዎሙ ለወሉድክሙ መጽሐፈ ሲራክ ፤ ወሰሎሞን ወመዝሙረ ዳዊት" ሲል የቤተ ክርስቲያኖችን ሕግ ያውጃል ።

በዚህም መሠረት አባቶች መምህራን እነዚህን መጻሕፍት በብዛት ይጠቀሙባቸው ነበር ፤ ሕዝቡም በግብረገብነት የታነፀ በሕግም የሚራመድ የነበረው ከልጅነቱ በዚህ መልክ ቢማርና በዚህም መንፈስ ቢመራ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ፤ ሳይነበብ የተተረጐመ ነው ።

ከዚህ ላይ ልናውቀውና ልንረዳው የሚያስፈልገን ቤተ ክርስቲያን ለአያሌ ዘመናት የኅብረተሰብኡን ልጆች በእውቀት በትምህርት አርማና ኮትኩታ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ፤ አርቀው የሚያስቡ መብትና ግዴታቸውን የተረዱ ፤ በሀገር ፍቅር የተቃጠሉ ፤ ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ነፃነት የሚ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞርአል




# "ከወፍ አእላፍ አብላኝ"

የሥጋ መብላት ጠባይ ካላቸው ከእንስሳት በቀር ሰዎች እንስሳት ወፎች በጠቅላላው በቃይ የሆነውን ነገር የሚመገቡ ሁሉ በገበሬ ድካምና ላብ ፤ በገበሬ ኃይል ተዘርቶ የተገኘውን የዘር ውጤት የሚመገቡ መሆናቸውን ይህ አነጋገር ሊያስረዳን ይችላል ። እንደተባለውም ገበሬው ዘር በሚዘራበት ጊዜ ራሱንና ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን እነዚህንም ጭምር እንደሚመግብ ስለሚያውቅ "ከወፍ አእላፍ አብላኝ" በማለት ወደ ፈጣሪው በእምነት እየጸለየ ዘሩን ይዘራል ። ሰው መሬት ሲያስረክብ ፈጣሪውን በማመን እንጂ ከሰጠው መሬት ዋስትና አይጠይቅም ። ይህም ብቻ አይደለም ድርቅ ያስቀርብኛል ጐርፍ ይወስድብኛል በረዶ ይመታብኛል ፤ አንበጣ ያጠፋብኛል ፤ አውሬና ከብት ይበላብኛል ። ይህ ሁሉ አደጋ የደረሰብኝ እንደሆን እደኽያለሁ ሳይል በእምነትና በተስፋ ዘርን ከመዝራት በቀር አይጠራጠርም ። እንዲያውም በልበ ሙሉነትና በመጽናናት ከወፍ አእላፍ ጠብቀህ አብላኝ እያለ ፈጣሪውን ተማጽኖ ዘሩን

ጸለየ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም ሁለተኛም ጸለየ ሰማዩም ዝናብ ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።" ይላል የያዕቆብ መልእክት ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፲፯-፲፰ ።

ዘራቸውን በእምነት ዘርተው የምሕረት ዝናብ ይጠባበቁ የነበሩት ገበሬዎች ዝናብ አግኝተው የዘሩት ዘር እንደበቀለላቸውና ምድርም አብቅላ መልካም ፍሬ እንደሰጠች ያስረዳናል ። ዛሬም ቢሆን ገበሬዎች እንደ ኤልያስ በእምነት ከጸለዩ ዝናብ ለዘር ፤ ጠል ለመከር እንደሚያገኙ ቃሉ ምስክር ነው ።



ብዙ ሲሳይ በበሬዎች ኃይል ነው (ምሳሌ ፲፬ ፡ ፬ ።) በሬ ... እየነዳችሁ በውኃ አጠገብ የምትዘሩ ብፁዓን ናችሁ (ኢሳ ፡ ፴፪ ፡ ፳)

በዘር ወራት የሚያስደንቀው ሌላው ሁኔታ ደግሞ ገበሬው ወደ ፊት በብዛትና በስፋት ምርት አገኛለሁ በሚል ተስፋ ከነቤተሰቡ እየተራበና እየተቸገረ ከጐተራውና ከያስቀመጠበት ልዩ ልዩ ጉስጉሻ ተበጥሮና ተጣርቶ የተቀመጠውን ንጹሕ ዘር አውጥቶ አርሶ ላለሰለ ወደ መሬት ከመበተን ወደኋላ አይልም ይህም የእምነቱን ጽንዐትና በፈጣሪው ላይ ያለው ተስፋ ከባድ መሆኑን ያሳያል ።

እምነት ታላቅ ኃይል እንዳለው ለማወቅ ቢፈለግ "ኤልያስ እንደኛው ሰው ነበር ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ

አንድ ሊቅ ደግሞ ስለ እምነት ጠቃሚነት ሲያስረዳ በማቴዎስ ፮ ፡ ፳፮ የተጠቀሰውን ምክንያት በማድረግ "ዐሐይ በየጊዜው እንደሚወጣልን ዝናብ በወራቱ እንደሚዘንምልን ተስፋ አድርገን እናምናለን ። ወደማናውቀው ከተማ ስንገባ ከኑዋሪዎቹ አንዱን አግኝ



www.ethiopianorthodox.org

ተን የምንፈልገውን ቤት አቅንቶ እንዲያሳየን እንጠይቀዋለን ። በሌላ በኩል ደግሞ በገበታው ዙሪያ ከበን ተዘጋጅቶ የሚቀርብልንን የዕለት ሲሳያችንን በእምነት እንመገባለን ይህም ማለት ምግባችንን ያቀረበልን ሰው መርዝ ቀላቅሎ እንደማይጨርሰን አምነን ያለፍርሃት እንበላለን ማለት ነው ። እምነት ባይኖር ኖሮ ግን ከመብላታችን በፊት ምግባችንን የሚመረምሩ ሐኪሞችን ሁል ጊዜ መጥራት ስለሚያስፈልገን ስንት የሚሰለች ነገር ባጋጠመን ነበር” ብሏል እንዳለውም ማንኛውም ሰው ያለ እምነትና ያለ ተስፋ ማረስ ፣ መቆፈር መዝራት ፣ መስራት ባልሆነለትም ነበር ።

ይህ በመሆኑ ማንኛውም ገበሬ ከወፍ እእላፍ አብላኝ እያለ በመጸለይ በእምነት ዘሩን ለምድር ያስረክባል ። ይህንንም ሲያደርግ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቃል ኪዳን አለ እሱም የሚከተለው ነው “በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ ፣ ብርድና ሙቀት በጋና ክረምት ቀንና ሌሊት አያቋርጡም” የሚለው ነው ። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፳፪ ።

ይህንን መሠረት በማድረግ ነው ገበሬው የዘሩን ወራት ጠብቆና ከጎተራው ንጹሕ ዘር አውጥቶ የሚዘራው ከዚህ ላይ ግን ልናስተውለው የሚገባ ነገር አለ ። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዘር አዘራር ለገበሬዎች ባስተማረበት ወቅት እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ ። ሲዘራ አንዳንዱ ዘር በመንገድ ላይ ወደቀ ወፎችም መጥተው በሉት ሌላውም ገበሬ በጭንጫ ላይ ዘራ ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ፣ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ። ሌላው ዘር ደግሞ በእሾህ ላይ ወደቀ መብቀሉን በቀለ እሾህ ወጣና አነቀው ሌላውም ገበሬ በለሰለሰ መሬት ላይ ዘራው በዚህ መሬት ላይ የወደቀውም ዘር በቅሎ ብዙ ፍሬ ሰጠ።

ይህ ከሆነ መዝራት ብቻ አይበቃም ማንኛውም ገበሬ ዘሩን በሚዘራበት ጊዜ መሬቱን መጀመሪያ አርሶና አለስልሶ መዝራት ይገባዋል እንጂ ለግብር ይውጣና ከማን አንሼ በማለት ባልለሰለሰ መሬት ላይ ቢዘራው ወፎች ይበሉታል ። በጭንጫ ላይም ቢዘራው መሬቱ ጥልቅ ስላልሆነ በፀሐይ ይደርቃል እሾሁን ሳይመነጥር ቢዘራው አንቆ ያስቀረዋል ። በለሰለሰ መሬት ላይ በእምነት ዘርቶ ቢጠባበቅ ግን የምሕረት ዝናብ ያገኝና የዘራው ይበቅልለታል ።

ያበቃቀሉም ሁኔታ በመጀመሪያ የተዘራው ዘር ይሞታል ይፈርሳል ይበሰብሳል እንደገና አዲስ አካል አግኝቶ ይበቅላል ። ይህ ሲሆን የገበሬው ዋና ሥራ የበቀለውን ቡቃያ ከብት እንዳይረግጠው መበጠቅ ፣ ቡቃያው የሚመገበውን ምግብ አረሙ እየተመገበ እንዳያቀጭጨው በየጊዜው ማረምና መኮትኮት ነው ። በመጀመሪያው ሥነ ፍጥረት ምድር ዘርን በየወገኑ እንድታበቅል እግዚየአብሔር ባዘዘው መሠረት ቡቃያን ያበቅላል ያፀድቃል ያሳድጋል በዚህ መንገድ ገበሬው ከወፍ እእላፍ አብላኝ እያለ በዘራውና ወጥቶና ወርዶ በላቡ ደክሞ ባስገኘው ምርት ሰዎችን ይመግባል እግዚአብሔርም በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ በነፋስ አሳድጎ ያስገኘውን በረከት ፍጥረትን ይመግባል ። ይህም ማለት ገበሬው የዘራው ዘር አንዱ ሠላሳ ፣ አንዱ ስልሣ ፣ አንዱ መቶ እንዲያፈራና እንዲበዛ ይባርክለታል ማለት ነው ።

የእግዚአብሔርን መጋቢነት በመንፈስ የተረዳው ነቢዩ ዳዊት “የሁሉ ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ አንተ እጅህን ትዘረጋለህ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ” ሲል ተናግሮአል ። መዝሙር ፻፵፬ ፣ ፲፭-፲፮ ።

እንዳባባሉ የፍጥረቱ ዓይን ሁሉ እሱን ተስፋ እንደሚያደርግ ነው የሚገልጸው እርግጥም ምግብ የማይሻ ሕይወት አይገኝም ይህም ማለት ገበሬው የዘራው ዘር ዝናም አግኝቶ መልካም ቡቃያ ሆኖ እንዲያድግለት ከዚያም በኋላ አስደሳች ሰብል እንዲሆንለት በመጨረሻም እንክርዳድና አርማሞ ያልተቀላቀለበት ንጹሕ ስንዴ እንዲያመርት ተስፋ ያደርጋል ። ምድርም ከዝናብ በምታገኘው ጠልና ልምላሜ ቡቃያን ትጐናጸፋለች እንስሳትም በዝናብ አመካኝነት የሚነጩትን ሣር የሚጐነጩትን ውኃ ለማግኘት ይመኛሉ ። ወፎችም ሣያርሱ ሳይቆፍሩ እግዚአብሔር ባዘነበው ዝናም የበቀለውንና በገበሬው ድካም የተገኘውን ሰብል ለዕለት ምግባቸው እንዲያገኙ ገበሬውን በዜማቸው ጠዋት ለሥራ እየቀሰቀሱ አምላክን ተስፋ ያደርጋሉ ።

ወፎች አይዘሩም ቢባልም ወጥተው ወርደው በድካማቸው ይመገባሉ እንጂ እግዚአብሔር ምግባቸውን እጐጆአቸው ድረስ እየወሰደ እንደማይጥልላቸው ማወቁ ይጠቅማል ። ስለዚህ ገበሬዎች ጠንክረው ማረስና መዝራት ይጠብቅባቸዋል ። በዚህ አኳኋን እግዚአብሔር በመጀመሪያው ስነ ፍጥረት የወሰነው ውሳኔ አይለወጥም ስለዚህ የሰጠው ፀጋ እንዳይጓደል ክረምቱን ለዘር በጋውን ለአዝመራ እያፈራረቀ ሰራተኛውን ገበሬ ሁሉ ያስደስተዋል ።

ይሁን እንጂ ገበሬ ዘር ሳይዘራ የዘራውንም ሳይንከባከብ የመከርን ወራት እየተጠባበቀ ብቻ ተስፋ ቢያደርግ ተስፋው ሁሉ ከንቱ ነው ወፎችም በተሰጣቸው ክንፍ ሣይበሩ ከአንድ ዛፍ ላይ ተተንጠልጥለው ምግባቸውን ለማግኘት ተስፋ ቢያደርጉ ሐሳባቸው የተሟላ አይሆንም በዚህ አኳኋን ምናልባት ሳይሠራ በየጊዜው ምግቡን ለማግኘት ተስፋ የሚያደርግ ቢኖር እርሱ እግዚአብሔርን ይፈታተነዋል ።

ስለዚህም ጠንክሮ በማረስ በመዝራት ፣ በመሰብሰብ የከበረውና በምድር ውስጥ በረከትን አግኝቶ እንጀራ የጠገበው ኢዮብ “እንጀራ ከምድር ውስጥ ይወጣል ሲል ተናግሮአል ። ኢዮ ፳፰ ቁ ፭” እንዳለውም እንጀራ የሚገኘው ከምድር ውስጥ ነው ሐብት ያለው ከምድር ውስጥ ነው በጠቅላላው ማዕድናት ሁሉ ተዳፍነው ያሉት በመሬት ማህጸን ውስጥ ነው ለምሳሌ ያደጉ አገሮች እየተባሉ የሚጠሩት ከምድር ቆፍረውና አርሰው ባገኙት ሀብት እንጂ ከሰማይ መና እየወረደላቸው አይደለም ። ስለዚህ ማንኛውም ገበሬ እንጀራ መጥ

ተከታዩን በገጽ ፳፪ ይመልከቱ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በዓለም ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ አስተዳደራቸውን ለማጠናከር ፣ የምእመናኑን ሕይወት በክርስቶስ ቃል አንድ ለማድረግ ፣ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ለተሠማሩት ካህናት የድካም ዋጋቸውን ለመክፈል የተግባረ እድ ሙያቸውን ያስተምራሉ ምእመናኑን ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴ በገንዘብ ኃይል የእርዳታ እጃቸውን ያስተባብራሉ መንፈሳዊ ዓላማቸው እንዲጠናከርም ስለቤተ ክርስቲያን ሕልውና አዘውትረው ያሳስባሉ ያስተምራሉ ።

ካህናቱም በዚሁ ሙያ ሠልጥነው በሚቋቋሙት የተግባረእድ ተቋሞች ውስጥ በመግባት የልማት ሥራዎችን ያካሒዳሉ ፣ ምእመናኑም መንፈሳዊ ዓላማቸውን በማጠናከር ቤተ ክርስቲያን በልማት ሥራዎች የታወቀችና የዳበረች ትሆን ዘንድ ከነሱ የሚፈለገውን የገንዘብ ፣ የዕውቀትና የቍሳቁስ እርዳታ በማድረግ የቤተ ክርስቲያናቸውን ዕድገት ያጠናክራሉ ።

ቤተክርስቲያንዋም “ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋል” ስትል ካህናቱ በምርት ውጤታቸው ተደስተው ቤተ ክርስቲያናቸውን በቅንነት እንዲያገለግሉና ምእመናኑም ከቤተ ክርስቲያን የሚፈልጉት መንፈሳዊ ግልጋሎት ያለችግር እንዲሟላላቸው ታደርጋለች ።

በአጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ተጠናክሮ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ያለ ችግር ሠርተው በደስታ ይኖራሉ ፤ አሠሪዎችም ቤተክርስቲያን የሰላም የፍቅርና የአንድነት መድረክ እንደመሆኑዋ ያለምንም ጭቅጭቅ በአገልግሎት ላይ ለተሠማሩ ካህናት የድካም ዋጋቸው እጥፍ ድርብ ቢሆን ይፈቅዳሉ ።

ዛሬ በጉልህ እንደሚታየው በዚህ ዓይነት በልማት ሥራ የተደራጁና በገቢው ያደጉ አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብና የቁሳቁስ ተራድኦ ለመስጠት በልማትና በሙያ ትምህርት እያጠናከሩአቸው ይገኛሉ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ አሠራር አንፃር በመነሳት ካህናትን በቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በእደ ጥበባት ሙያ እያሰለጠነች ራስዋን ችላ ለመኖር ጥረት እያደረገች ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የፈለግነው ግን በሲዳሞ ሀገረ ስብከት በአዋሳ ከተማ የሚገኘው የካህናት ማሰልጠኛ በልማት ሥራ ባሳየው እንቅስቃሴ ፺፪ ኩንታል በቆሎ ማምረቱና ከጓሮ አትክልት ጠቃሚ ውጤት አስገኝቶ በመታየቱ እንቅስቃሴውን ለሌሎች ለማሳወቅ ነው ።



ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ
የሲዳሞ ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ይህ የልማት ውጤት የተገኘው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርተሎሚዎስ [illegible] በሚያሳርጉት ትጋት ፤ በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ አስተባባሪነት ፣ በት/ቤት ርእስ መምህር እስጢፋኖስ ተመስገን ተቆጣጣሪነት በደብሩ የሚገኙት መደበኛ ካህናትና የሴሚናሩ ተሳታፊዎች በሚያደርጉት በጐፈቃድና የሥራ ትብብር የልማቱ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ በመሔድ ከዚህ የእርሻ ሙከራ ፩፻፱ ኩንታል በቆሎ ለማምረት መቻሉን መልአከ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ አብራርተዋል ።

በሲዳሞ ሀገረ ስብከት የተቋቋመው የካህናት ማሰልጠኛ “አዋሳ ” ሐይቅ አጠገብ የሚካሔድ በመሆኑ ከዚህ የበለጠ የምርት ውጤት ለማግኘት እንደሚቻል የሁላችንም እምነት ነው ።

ከመልአከ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ አገላለጽ ለመረዳት እንደሚቻለው ለዚህ የካህናት ማሰልጠኛ የልማት አገልግሎት የሚውል ከ፲ ሔክታር በላይ የሚሆን የእርሻ መሬት ሲኖረው ፣ በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. የአዝመራ ወቅት ለሙከራ የተዘራው የበቆሎ ሰብል ፩፻፱ ኩንታል ተመርቷል ።

በጓሮ አታክልት ረገድም እንደካሮት ፣ ቀይስርና ቲማቲም የመሳሰሉት በየዕለቱ ገቢ በማስገኘት ውጤታቸው ተደምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ፲ ሺህ ብር በላይ የገንዘብ ገቢ ለማስገኘት መቻሉ እጅግ የሚያስደስት ነው ።

ይህ በአዋሳ የተቋቋመው የካህናት ማሰልጠኛ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ለልማቱ ሥራ መጠናከር ያላቸው ዝንባሌ የማያቋርጥና ጠንካራ በመሆኑ ካህናቱ በማሰልጠኛው ውስጥ ከቀለም ትምህርታቸው ጋር የእደ ጥበባትን ሙያ በማጣመር ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት ለሌሎች ምሳሌ እየሆነ እንደሚሔድ ተስፋችን የማያቋርጥ ነው በማለት መልአከ ምሕረት ጳውሎስ አስረድተዋል ።

በአዋሳ የተገኘው የምርት ውጤት ለሙከራ ያህል በ፬ ሔክታር መሬት ላይ ተዘርቶ ይህን አስደሳች ምርት በማግኘታችን ከዚህ ደስታ በመነሳት በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ማለት በያዝነው የአዝመራ ዘመን ከዚህ በበለጠ እንደምናመርትና የተለያዩ የአትክልት ዓይነቶችን በመትከል የምርት ውጤታችንን ከፍ እናደርጋለን



www.ethiopianorthodox.org

በማለት መልአከ ምሕረት እቅዳቸውን ገልጸዋል ።



መልአከ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ
የሲዳሞ ሀ/ ስብከት ሥራ አስኪያጅ

መልአከ ምሕረት በአስተያየት መልክ ሲያብራሩ "በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ልማት እንዲስፋፋ የሁላችንም ምኞት ነው ፣ እስከ አሁንም በአንዳንድ ቦታዎች ተጀምረው ገቢ በማስገኘት ጭልጭል የሚሉትም በይበልጥ እንዲጠናከሩ ሊታሰብላቸው የሚገባ መሆኑን እናምናለን ፣ ነገር ግን ከቁጥጥር ጉድለት የተነሳ ከገቢአቸው ወጭአቸው እያመዘነ እንደሚሔድ ይታያል ፣ ይህ ከሆነ አመረትን ከማለት አለማምረቱ ይሻላል ፣ ይህ እንዳይሆን ለልማት ሁሉም ኃይሉን ፣ ዕውቀቱንና ገንዘቡን ያስተባብር ፣ የተጀመረው ልማትም ተጠናክሮ የበለጠ ውጤት እንዲያስገኝ የበላይ ቁጥጥር አይለየው ፣ ይህ ከሆነ በሯቱ የካህናት ማሰልጠኛዎች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደሪያ የሚበቃ ምርት ሊመረት ይችላል ብዬ እገምታለሁ" ብለዋል ።

እኛም ስለልማት እድገት ደጋግመን እንዳሳሰብነውና አሁንም መልአከ ምሕረት ጳውሎስ በሰጡት አስተያየት መሠረት ልማት ይስፋፋ. የተጀመረው ይጠናከር የተጠናከረው ገቢው በማንም እንዳይበዘበዝ ሕጋዊ ቁጥጥር አይለየው እንላለን ።

በሌላ በኩል ከእርዳታ ሰጭ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች የሚገኘው የተራድኦ ገንዘብ በሯቱ የካህናት ማሰልጠኛዎች ቋሚና ዘለቄታ የሚኖረው ማምረቻ እንዲቋቋም የበለጠ ጥረት ይደረግበት ።


በሲዳሞ በአዋሳ ሐይቅ ፣ በጎጃም በጣና ሐይቅ ፣ በሸዋ በዝዋይ ሐይቅ አጠገብ የተቋቋሙት ማሰልጠኛዎች የገቢ ምንጭ እያሳዩ ናቸው ቢባልም አጥጋቢ አይደሉም ።

ስለሆነም የበለጠ የምርት ውጤት እንዲያሳዩ አሠሪዎችና ሠራተኞች የተባበረ ኃይላቸውን ያጠናክሩ ፣ ልማት በቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ በገንዘብና በሚፈለገው ሁሉ እርዳታ የሚያደርገው ክፍልም የተጀመሩት የልማት ሥራዎች በበለጠ ተጠናክረው ራሳቸውን በራሳቸው ለመርዳት ይችሉ ዘንድ የተለመደው እርዳታ አይለያቸው ።

የቀለም ትምህርቶች ከእደ ጥበባት ሳይለያዩ ካህናት በዚህ ሙያ እንዲሠለጥኑ አሠሪዎች ሠራተኞችና ምእመናን ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ያስተባብሩ ።

በሲዳሞ የታየው ውጤት አኩሪ ነው ብንልም ከዚህ የበለጠ ውጤት እንዲያሳይ ይታሰብበት እንላለን ።

በለጠ አበበ



በሲዳሞ የካህናት ማሠልጠኛ የተመረተው የበቆሎ ምርት
በተሸጠበት ወቅት በመኪና ሲጫን ።

## ቤተ ክርስቲያንና ....

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ጥሩ ዜጎችን ስታበረክት ኑራለች ።

ምንጊዜም ቢሆን ከሃይማኖት ፣ ከግብረ ገብነትና ከሀገር ፍቅር ጋር የሚሰጥ ፍልስፍና ጥልቀትና ምጥቀት ይኖረዋል ። በዚህ እረገድ ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰብኡ ፣ ኅብረተሰብኡም ለቤተ ክርስቲያን ተገቢውን አስተዋጽኦ በማበርከት ለዘመናት ኑረዋል ፣ ወደፊትም ይኖራሉ ፣ "ጥርስና ከንፈር ቤተ ባበር ያምር" እንዲሉ አንድ ሀገር በባሕል ፣ በታሪክና በማኅበራዊ ኑሮ ለሚያደርገው መሻሻል መንፈሳዊውም ሆነ ሆነ ሥጋዊው ድርጅት በመተባበር ለኅብረተሰብኡ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ነው ። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰብኡ ፊደል ሠራዊትን ለማዳረስ ለአያሌ ዘመናት አቅሟ በፈቀደላት መጠን ስታስተምር ኑራለች ፣ በአሁኑ ጊዜ ግን መንግሥት መሠረተ ትምህርትን ለሰፊው ሕዝብ ዳር እስከዳር ለማዳረስ ባለው ከፍተኛ ምኞትና ዓላማ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተከፍቶ ሥራው በመጣደፍ ላይ ይገኛል ፣

ተከታዩን በገጽ ፲፯ ይመልከቱ



# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

የአንድ ሀገር ህልውና ምንጩና ይዘቱ ቤተሰብ ነው ፤ ይህም በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተ እንደሆን ጥቅሙ የበለጠ ይሆናል የቤተሰብ አኗኗር ሁኔታ የሚያውቅ የአካባቢን የሀገርንና የዓለምን ሁኔታ ለማጥናት ወይም ለማስተዳደር አይሳነውም ማለት ይቻላል ። ይህም ማለት በስመ ቤተሰብነት የተመሠረተው ሳይሆን ትክክለኛውን የቤተሰብ አኗኗር ዘይቤ የተከተለ እንደሆነ ነው ። ቤተሰብ ለህብረተሰብ ሁሉ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን የሚወሰነውም የቤተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ በመልካም ሥነ ምግባር የታነጸ እንደሆን ነው ። በዚህ ሁኔታ ከተመሠረተው ቤተሰብ ብዙ መልካም ውጤቶችን ለማግኘት ይቻላል ። የዚህ ዓይነቱም ቤተሰብ ተጠሪነቱ በሁሉም በኩል ቢሆን አያሳፍርም ። ለዚህም ሁሉ እንዲበቃ የሚያደርገው የመልካም ቤተሰብ አኗኗር ውጤት ነው ።

ስለዚህም እንደነዚህ ያሉትን ቤተሰቦች ስናስተዋውቃችሁ አርአያነታቸው ጠቃሚ ትምህርት እንደሚሰጥ በመተማመን ነው ።

በዚህ ጽሑፍ የምናስተዋውቃችሁ ጋብቻቸውን ከመሠረቱ ፲፪ኛ ዓመታቸውን ከያዙት ከአቶ ተሰማ ቅጣውና ከባለቤታቸው ከወ/ሮ መዓዛሽ መኩንን እንዲሁም ልጆቻቸውን ጭምር ነው ።

አቶ ተሰማ ፵፫ ዐመት ዕድሜ ያላቸው ሲሆኑ በዚህ ዕድሜአቸውና የጋብቻ ዘመናቸው የአራት ልጆች አባት ናቸው።

አቶ ተሰማ እንዴት ወደ ጋብቻ ዓለም እንደመጡ ለጠየቅናቸው ሲመልሱ ኑሮዬን በጋብቻ ዓለም መሥርቼ ለመኖር ካበቃኝ ዋነኛ ነገር የብቸኝነትን ኑሮ መሰልቸትና የሚመጣብኝን ችግር ሁሉ ለብቻዬ መቋቋም አለመቻሌን ደህና አድርጌ ከተረዳሁት በኋላ ነው ። ወጥቼ ስመለስ የተዘጋውን በር ከፍቶ ለመግባት እጨነቅ ነበር ። ከፍቼም ስገባ የሚሰማኝ ጭንቀትና የሃሳብ ውጣ ውረድ ይህነው አይባልም በተለይማ አሞኝ ወይም ደክሞኝ ስገባ የደረሰብኝን ሁሉ ለማውራት ቃላት ያጥሩኛል የሚያሳዝነው ደግሞ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዚሁ ወቅት በሽታ እጅግ ያጠቃኝ ነበር ይኸውም ካለፈው ኑሮዬ ሳሳልፍ ከቆየሁት ሁሉ ጥቂቱ ነው።

አሁን ያለሁበትንም በአጭሩ ለመግለጽ ቢያስፈልግ ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ጋብቻ ጉዳይ ለጻፋለት በመንፈስ ተመልቶ ሲመልስ ሴት ባልዋ በህይወት ሳለ የታሰረች ናት ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት ። ፩ኛ ቆሮ. ፯ ፡ ፴፱ ደግሞም የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ያለ ይመስለኛል ብሎ በማረጋገጥ በጻፈው ከታቡ ለወንዱም ቢሆን እንዲሁ ነውና በሀገር ቤት ያገባኋት የሕግ ሚስቴ ስለሞተችብኝ ብዙ ጊዜ ራሴን ለብቻ ለማኖር ካደረኩት ትግል (ግብ ግብ) በኋላ አሁን አብሬ ያለኋትን ወ/ሮ



አቶ ተሰማ ቅጣው ከቤተሰቦቻቸው ጋር

መዓዛሽ መኩንን በሕግ ለማግባት ቻልኩ ። አሁን ፲፪ ዓመታችንን ይዘናል በዚህምጊዜውስጥ ከላይእንደተገለጠው አራት ልጆችን አፍርተናል ከዚህ በፊት በአንድ ሰው እስትንፋስ ሰጥማ የነበረ ችው ደሳሳጐጆዬ አሁን ይኸው በስድስት ሰዎች እስትንፋስ ተሞልታለች በዚህም ያለብኝ ጭንቀት ብስጭት ሌላውም ችግሬ ሁሉ ተወግዶልኛል ። አሁን ያለሁበት የጋብቻሕይወት በፊት ከነበረኝ የጋብቻ ሕይወት ጋር ሲወዳደር የሚሰማኝ ስሜት የበፊቱ እኔ ስለጋብቻ ብዙ ባላጠናሁበት ፣ በቤተሰቦቼ ሥር ባለሁበትና ችግርንና ብቸኝነትን ለይቼ ባለወቅሁበት ጊዜ የተደረገልኝ እንጂ እኔ ያላሰብኩለት ኑሮ ስለሆነ ይመስለኛል ባለቤቴ በሞት ከመለየቷ በስተቀር የማውቀው የለኝም ። ከዚያ በኋላ ያለው ህይወቴ ግን በብዙ ዓይነት በሽታዎች ፈተና ያየሁበትና ለበሽተኞችም የሚያስፈልገው እርዳታ በብቸኝነቴ ምክንያት ስላልተደረገልኝ ሁሉም ተጨማምሮ ደህና አድርጐ ስለደቆሰኝ አለመቻሌን በመረዳት እንደገና ትዳርን እንድመሠርት አስገደደኝ ይኸውም ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ እንዳልሆነ ጠይቄ ከተረዳሁ በኋላ ነው ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚለውን የፈጣሪን ቃል ሁሉም ሰው በማክበር ጠብቆት ይኖራል ይኸውም በእምነት ውስጥ ያሉ ብቻ ባይሆንም የተፈጥሮ ሕጐች ሁሉ በህብረተሰቡ ዘንድ እየተጠበቁ ይኖራሉ በዚህም ዓለማችን በሕዝብ ለመሞላት ምክንያት የሆነው ቤተሰብ መሆኑ አይዘነጋም እውነትም ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም እንዱ ቢወድቅ ሌላው ያነሳዋልና ነው እርዳት ከሌለው ግን ወድቆም ይቀራል ለማለት ይቻላል ። ስለዚህ እኔም ትዳር ላልያዙ ሁሉ በራቸውን ዘግተውና ከተዘጋው ቤት ውስጥ ሆነው የሚመጣውን ችግርም ሆነ ደስታ በብ



www.ethiopianorthodox.org

ቸኝነት ለመወጣት ከመሞከር ይልቅ የተዘጋውን ቤት በቀና መንፈስ ለትዳር ከፍቶ ደስታንም ሆነ መከራን ከቤተሰብ ጋር አብሮ መካፈሉ በጣም የሚሻል ይመስለኛል ።

ለሰው በቤተሰብ ውስጥ ከሚገኝ ሕይወት ጋር በእንግድነት የሚኖሩትን ዓለም ቢያሳልፉአት ከዚህ የሚበልጥ ደስታ የለም ሲሉ አቶ ተሰማ ስለቤተሰቦቻቸው ያላቸውን አስተያየትና ማጠቃለያ ሃሳባቸውንም ጭምር በአጭሩ ሰጥተውናል ። እናመሰግናቸዋለን ይህም ለሌሎች መልካም አርአያነትን እንደሚሰጥ አያጠራጥርም ።

የሰው ልጅ በዚች ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ኑሮውን የሚወስንበት ደረጃ በሚመሠርተው ቤተሰብ አማካኝነት መሆኑ ይታወቃል በዚያም የኑሮን ትርጉም በበለጠ የሚረዳበት እራሱን የሚመረምርበትና ለሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦች ሲል ያልተስተካከሉ ጠባዮች ቢኖሩ የሚያርምበትና ራሱን የሚገዛበት ወቅት ይሆናል ። ከዚህ በመነሳቱ በሚያደርገው ድርጊት ወይም በሚሄድበት ቦታ ሳይቀር ለቤተሰቦቹ ከሚያደርገው እንክብካቤና ኃላፊነት ሁሉ ያነሰ አይሆንም። በሁሉም ዘንድ ኃላፊነት ቢጣልቢትም የሚያሳፍር አይሆንም ።

ለዚህ ሁሉ ኃላፊነት የሚያበቃውን የቤተሰብ ሁኔታ ማወቅ ኃላፊነትንም ለመውሰድ አለመዘግየት ከመልካካም ቤተሰቦች እንደተረዳነው ከሆነ ብልህነት ነው ።

# ከወፍ አፅላፍ ....

ከገጽ ፳ የዞረ

ገብ ከፈለገ አገሩንም የዳቦ ቅርጫት ለማረግ ከተነሳ ጠንክሮ ምድርን እያረሰ መዝራትና ማምረት አለበት ። ቡቃያን ማብቀል ማሳደግ ዛላን መስጠት በዛላውም ላይ ሰብልን ማድረግ ግን የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ ማንኛውም ሰው በዚህ ሊያስብ አይገባውም ።

እንግዲህ ስለ ዘሪው ገበሬና ስለዘር አበቃቀል ተመልክተናል መምህራን የሆንን ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በምዕመናን ሕይወት ላይ በእምነት እንድንዘራ ይፈለግብናል ። ለምሳሌ ቡቃዮች ከሚያንዣብበው ከጥቁር ደመና የሚወርደውን የዝናብ ጠብታ ተቀብለው ይበቅላሉ ለምልመውም ያፈራሉ እንደዚሁም ምዕመናን የእግዚአብሔርን ቃል ከተመገቡ አዲስ ሕይወትንና የልብ መለወጥን ስለሚያገኙ በመንፈስ ያድጋሉ የመንፈስ ፍሬም ያፈራሉ፡ ይህም እንዲሆን ጠንካራ የሆኑ የወንጌል መምህራን ያስፈልጋሉ መምህራንም ስንል ራሳቸው እሾህ ሳይሆኑ የእግዚአብሔርንም ቃል በእሾህ ላይ የማይዘሩ ራሳቸውም የለሰለሱ ሆነው በለሰለሰውና እራሳቸውም እያለሰለሱ የእግዚአብሔርን ቃል ከዘሩ በቅሎ መልካም ፍሬ ይሰጣል ። ከእኔ የሚወጣው ቃል የምሻውን ያደርጋል የላኩትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም ስለሚል ቃሉን በሚገባ እንዝራ የቤተ ክርስቲያን አላማዋ ይህ ነውና ።

አለቃ ነብየ ልዑል ዮሐንስ

# ሰላም ለሁላችሁ ...

ከገጽ ፲፫ የዞረ

ይሁን እንጂ ዓለም በጠቅላላው "ሰላም ሰላም" እያለ ስለጮኸ ሰላም ሊገኝ አይችልም ። ዓለም በራሱ ፈቃድና ምኞት ብቻ ሰላም ሊፈጥር አይችልም ምክንያቱም ሰላም የመንፈስ ፍሬ እንጂ በሰው ልጆች ምኞትና ፍላጎት ብቻ ሊወሰን የማይችል ነገር ስለሆነ ነው ።ገላ ፭ ።

ለዚህ ነው ሰላምን ይሻሉ እርሱም አይገኝም በማለት ነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢት የተናገረው ሕዝ. ፯. ፳፭ ። ስለዚህ ዓለም እስኪሰነጠቅ ድረስ ሰላም ሰላም እያለ ቢጮኸ ሰላም ሊገኝ አይችልም ። ነገሩ ሰላም ሳይኖር ሰላም ሰላም ይላሉ ። በማለት ኤርምያስ እንደተናገረው ነው። ኤር. ፮.፲፬ ።

ይህም ሰላምን አትፈልጉ ማለት አይደለም ። ሰላምንስ እንድንፈልግ ታዝናል ።እግዚአቦሔር በነቢዩ እንደበት አድሮ ሲናገር የሀገርን ሰላም ፈልጉ ብሏል ። ኤር. ፳፱.፯ ።

ኢሳይያስም ለሰላም ፈላጊ ከፍተኛ ግምት በመስጠት ሰላምን የሚያወራ እጅግ ያማረ ነው ። ሲል ይናገራል ኢሳ. ፶፪.፯ እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስም ሰላም የሚቆምበትን እንከተል እያለ ይመክረናል ። ሮሜ. ፲፬. ፲፱ ።

ስለዚህ ሰላምን መፈለግ የእምነታችን ግዴታ ነው ። እንግዲህ ከዚህ በላይ በርከት ያሉ መረጃዎችን በመጥቀስ ለማስረዳት እንደሞከርነው ሰላም በጠቅላላው የዓለም ሕዝብ ጥያቄ ከመሆኑም በላይ የሚገኘውም በጠመንጃ አፈሙዝ ሳይሆን መሪዎች ስለሰላም በሚያደርጉት ጥረትና ረዳትነት መሆኑን በእግዚአብሔር አስተውለናል ።

እግዚአብሔርን ብናውቅ ፀጋና ሰላም ይበዛልናል ፪ኛ ጴጥ. ፩.፪ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ በእኔ ስላችሁ ግን ሰላም አላችሁ ዮሐ. ፲፮

መ/ ስማቸው ንጋቱ

# ምን እንርዳዎ ?

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ክርስቲያናችን የሥርዓት መጽሐፍ ፍትሕ መንፈሳዊም በአንቀጽ ፳፬ አንቀጸ ጋብቻ ላይ ለሴት ልጅ ማጫ መስጠት ተገቢ መሆኑ የተገለጸ ስለሆነ እርስዎም ይህንኑ ተረድተው ቀደም ብለው በመዘጋጀት የሚያጨአትን ልጅ ጌጣጊጥ ለማሟላት ከአሁኑ እንዲዘጋጁ እንመክርዎታለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቁ. 116616
የመል. ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ